# በቀላል መልኩ የተዘጋጀ የተውሒድ መፅሐፍ

# التوحيد الميسر

አዘጋጅ / ዓብደሏህ ቢን አሕመድ
አል ሑወይል

ተርጓሚ ዓብዱረሒም ሙሳ ሐሰን

عبد الله بن أحمد الحويل

ترجمة/عبد الرحيم موسى حسن الأثيوبي

# ማውጫ


የተውሂድ ትርጉም፡-........................................................................................................ 7

የተውሂድ ዓይነቶች፡- ..........................................................................................................5

የተውሂድ ወሳኝነትና ደረጃው፡- .............................................................................................8

ሽርክ እና ዓይነቶቹ፡- .......................................................................................................... 19

የእስልምናን እምነት የሚያበላሹ ነገሮች፡- ...............................................................................26

ጣዖት፡-.....................................................................................................................................28

ክህደት፡- ..................................................................................................................................30

ንፍቅና/አስመሳይነት/፡- ..........................................................................................................33

ወላእና በራእ (መውደድና መጥላት) በኢስላም ፡-.........................................................................34

አል -ኢስላም ወይም እስልምና፡-.............................................................................................. 36

የእስልምና መሰረቶች፡-............................................................................................................ 36

የእምነት ማዕዘናት.......................................................................................................................38

በቀደር ማመን፡- ......................................................................................................................... 40

በጎ ስራ፡-......................................................................................................................................42

የአምልኮ ምንነት፡-.......................................................................................................................43

የአምልኮ መስፈርቶች ..................................................................................................................... 44

የውዴታ ዓይነቶች፡-........................................................................................................................ 46

ፍርሐት፡- ........................................................................................................................................47

ተስፋ፡- ............................................................................................................................................ 49

ተወኩል ወይም መመካት፡- ............................................................................................................... 49

ዱዓ ወይም ልመና፡-......51

ሩቅያ/የበሽታመከላከያ/፡-......52

ተማኢም(ህርዞች)፡-......53

በረከትን ወይም ረድኤትን መፈለግ፡-......54

ተወሱል ወይም መጠጋት፡-......56

እርድ፡-......57

ነዝር (ስለት)፡-......58

እርዳታንና ጥበቃን መለመን፡-......59

ምልጃ፡-......60

መቃብርን መዘየር/መጎብኘት/፡-......61

ድግምት፡-......62

ጠንቋይና አዋቂ ነኝ ባይ፡-......64

በገድ ማመን፡-......65

ተስፈኝነት፡-......68

ከዋክብት ለምን ተፈጠሩ ?......69

ይስሙላ፡-......70

መሐላ፡-......75

እንዲህ ቢሆን(ባይሆን) ኖሮ ይህ ባልሆነ ነበር ማለት፡-......77

ግዜን መሳደብ እና መተቸት፡-......78

ፈጠራ፡-......79

## የአዘጋጁ መቅድም

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው፡፡

የዓለማት ፈጣሪ ለሆነው አላህ ምስጋና ይገባው የአላህ እዝነትና ሰላም የነቢያት መደምደሚያ በሆኑት በታላቁ መልእክተኛ በሙሐመድ እና በተከታዮቻቸው ላይ ይስፈን።
በመቀጠልም፡- አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ፍጹም ለእርሱ ብቻ የተሰራን መልካም ስራ እንጂ አይቀበልም በመሆኑም፡-
ይህ መጽሐፍ የተውሂድን ምንነትና ወሳኝነት እንደዚሁም የሽርክን(በአላህ የማጋራትን) አደገኝነትና ዓይነቶቹን በሚገባ የሚያብራራ እና የተውሂድን መሰረታዊ ነጥቦች በቀላሉ ለአንባቢያን የሚያስጨብጥ እጥር ምጥን ያለ ወሳኝ መጽሐፍ ነው።
በዚህም መጽሐፍ ተጠቃሚዎች ያደርገን ዘንድ አላህን እለምናለሁ

**አዘጋጅ/ አብዱሏህ አል-ሁይል**

## የተርጓሚው ማስታወሻ፡-

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው፡-

ሰዎች ስለ ፈጣሪያቸው ማወቅና እርሱን ብቻ መገዛት ከምግብና ከመጠጥ እንደዚሁም ከሌሎች እውቀቶች ሁሉ ይበልጥ ለእነርሱ ወሳኝና አንገብጋቢ ጉዳይ ነው በዚህም መሰረት ይህ መጽሐፍ ከአርብኛ ወደ አማርኛ ቋንቋ ቢተረጎም አረበኛውን የማይረዱ ወንድሞች የተፈጠሩለትን አላማ ከትርጉሙ መረዳት እንደሚችሉ ተስፋ በማድረግ በአላህ ፍቃድ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተርጉሜ ለወገኖቼ ሳቀርብ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል ይሁን እንጂ ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት አይቀርምና በትርጉሙ ዙሪያ የሚገኙ ስህተቶችንና አስተያየቶቻችሁን በ(abuabdelah787@gmail.com (ወይም በ 0503655174 ሞባይል አድራሻችን ስታደርሱልን በታላቅ ክብርና ደስታ እንቀበላለን

ተርጓሚ/አብዱረሂም ሙሳ ሐሰን

**የተውሂድ ትርጉም፡-**

ተውሂድ ማለት በቋንቋ አንድን ነገር ብቸኛ ማድረግና መነጠል ሲሆን ሃይማኖታዊ ትርጉሙ ደግሞ አላህን በሶስቱ የተውሂድ አይነቶች ማለትም፡- በጌትነቱ፤ በአምላክነቱ ፤ በስሞቹና በባህሪያቱ አጋርና አምሳያ የሌለው ብቸኛ አምላክ መሆኑን ማመን ማለት ነው።

## የተውሂድ ዓይነቶች፡-

ተውሂድ በሦስት ይከፈላል እነሱም፡-

1ኛ- ተውሂዱል - ሩቡቢያ እሱም፡- አላህ ሰማያትንና ምድርን፤ ሰዎችንና ጅኖችን፤ እንደዚሁም ማንኛውንም ፍጥረታት ሲፈጥርና ሲያስገኝ አማካሪና ተባባሪ ሳይኖረው ሳያስፈልገውም በብቸኝነት የፈጠረና ያስገኘ መሆኑን ማወቅና ማመን ነው።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ أَلا لَهُ الْخَلْقُ وَالأَمْرُ تَبَارَكَ اللَّهُ رَبُّ الْعَالَمِينَ }الأعراف: 54)

" አስተውሉ! የመፍጠርና የማዘዝ ስልጣን የእርሱ(የአላህ) ብቻ ነው። የዓለማት ፈጣሪ የሆነው አላህ ክብሩ የላቀ ነው " (አል-አዕራፍ፡54)

አላህ በሌላ አንቀፅ ላይም እንዲህ ይላል፡-

{ وَلِلَّهِ مُلْكُ السَّمَاوَاتِ وَالأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا يَخْلُقُ مَا يَشَاءُ وَاللَّهُ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِير } ( المائدة:17).

" የሰማያትና የምድር የመካከላቸውም ንግሥና የአላህ ብቻ ነው፡፡ የሚሻውን ይፈጥራል፡፡ አላህም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው " (አልማኢዳ፡17)

2ኛ- ተውሂዱል- ኡሉሂያ እሱም አላህ በአምላክነቱ ብቸኛ መሆኑን ማወቅና ማመን ነው። ይህም ሊረጋገጥ የሚችለው አማኞች የሚሰሯቸውን መልካም ስራዎች ለምሳሌ፡- ሶላትን፤ ፆምን፤ ሐጅን፤ ፀሎትን፤ ስለትን፤ ውዴታንና

የመሳሰሉትን መልካም ስራዎች ሲያከናውኑ ፍጹም ለአላህ ብቻ አድርገው ሲሠሩ ብቻ ነው።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَاعْبُدُوا اللَّهَ وَلا تُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا } ( النساء :**36**)

“ አላህንም ተገዙ በእርሱም ምንንም አታጋሩ ” (አል-ኒሳእ፡ 36)

አላህ በሌላ አንቀፅ ላይም እንዲህ ይላል፡-

{ وَمَا أَرْسَلْنَا مِنْ قَبْلِكَ مِنْ رَسُولٍ إِلا نُوحِي إِلَيْهِ أَنَّهُ لا إِلَهَ إِلا أَنَا فَاعْبُدُونِ }( الأنبياء :**25**) .

“ ከአንተ በፊት ማንኛውንም መልእክተኛ አላክንም እነሆ ከእኔ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም። ስለዚህ እኔን ብቻ ተገዙ የሚል መለኮታዊ ራዕይ ወደ እርሱ ያወረድን ቢሆን እንጂ ” (አል-አንቢያእ፡25)

3ኛ- ተውሂዱል- አስማኢ ወሲፋት እሱም አላህ በስሞቹና በባህሪያቱ ብቸኛ መሆኑን ማወቅና ማመን ማለት ነው። ይህም የሚረጋገጠው አላህ እርሱ ለራሱ ያፀደቃቸውን ስሞቹንና መልካም መገለጫ ባህሪያቱን እንደዚሁም በመልእክተኛው አማካኝነት የፀደቁትን ስሞቹንና ባህሪያቱን በፍጡራን ስሞችና ባህሪያት ሳናመሳስል ወይም ትርጉሙን ሳናዛባ ወይም ትርጉም አልባ ሳናደርግ በቀጥታ ቃሉ በሚሰጠው ትርጉም መሰረት ስናምን ብቻ ነው።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

**{** لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ وَهُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرِ} ( الشورى: **11**)

“ እርሱን (አላህን) የሚመስል አንድም የለም እርሱም ሰሚና ተመልካች ነው ”(አሹራ፡11)

አላህ በሌላ አንቀፅ ላይም እንዲህ ይላል፡-

{ وَلِلَّهِ الأَسْمَاءُ الْحُسْنَى فَادْعُوهُ بِهَا وَذَرُوا الَّذِينَ يُلْحِدُونَ فِي أَسْمَائِهِ سَيُجْزَوْنَ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ } ( الأعراف: **180**).

" አላህም መልካም ስሞች አሉት። በነዚያም መልካም ስሞቹ ለምኑት። እነዚያንም ስሞቹን የሚያጋድሉና የሚያጣሙ ሰዎችን ተዋቸው ይሰሩት የነበሩትን ነገር በእርግጥ ይመነዳሉ "(አል-አዕራፍ፡ 180)

<u>ወሳኝና ጠቃሚ ነጥቦች፡-</u>

1- እነዚህ ሦስት የተውሂድ ክፍሎች ከፍተኛ ትስስርና ተዛምዶ ያላቸው በመሆኑ በአንዱ አምኖ በሌላው መካድ በሁሉም እንደመካድ ይቆጠራል።

2- በአላህ መልዕእክተኛ /ﷺ/ ወቅት የነበሩት ከሃዲያን የሁሉ ነገር ፈጣሪ ፤ ሲሳይን ሰጪ ፤ ሕይወት የሚሰጠውና የሚነሳው አላህ ብቻ መሆኑን ጠንቅቀው ያውቁና ያምኑ ነበር። ይሁን እንጂ ከአላህ ውጭ የሆነን አካል ያመልኩ ስለነበር ይህ እምነታቸው ሙስሊሞች ሊያሰኛቸው አልቻለም።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ قُلْ مَنْ يَرْزُقُكُمْ مِنَ السَّمَاءِ وَالأَرْضِ أَمَّنْ يَمْلِكُ السَّمْعَ وَالأَبْصَارَ وَمَنْ يُخْرِجُ الْحَيَّ مِنَ الْمَيِّتِ وَيُخْرِجُ الْمَيِّتَ مِنَ الْحَيِّ وَمَنْ يُدَبِّرُ الأَمْرَ فَسَيَقُولُونَ اللَّهُ فَقُلْ أَفَلا تَتَّقُونَ } (يونس:**31**) .

"ከደመና ባወረደው ዝናብ አዝርእቶችን ከምድር በማብቀል ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማነው? መስሚያዎችንና መመልከቻዎችን የፈጠረላችሁስ ማነው?፤ ሕይወት ያለውን ሕይወት ከሌለው የሚያወጣና ሕይወት የሌለውንም ሕይወት ካለው የሚያወጣስ ማነው? ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብረውስ ማነው? በላቸው በእርግጥም አላህ ነው ይላሉ። (ታዲያ

ይህን ሁሉ ማድረግ የሚችለው አላህ ብቻ መሆኑን እያወቃችሁ ሌላን አካል በእርሱ እንዴት ታጋራላችሁ? ) አላህን አትፈሩምን? በላቸው ” (ዩኑስ፣ 31)

3-የመልእክተኞች የመጀመሪያ ጥሪ ተውሂዱል ኡሉሂያ(አላህን ብቻ ተገዙ) የሚለው ቁም ነገር ነው። ምክንያቱም ማንኛውም አምልኮ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ተውሂዱል ኡሉሂያ ዋና መሰረት ስለሆነና እሱ ካልተረጋገጠ ተቃራኒው/ ሺርክ/ መኖሩ አይቀሬ ስለሆነ ነው።

4- በመልእክተኞችና በወገኖቻቸው መካከል አለመግባባትና ጭቅጭቅ የተፈጠረውም በዚሁ የተውሂድ ክፍል ነበር። ስለዚህ ይህን የተውሂድ ክፍል ማወቅና በሚገባ መረዳት የማንኛውም ሰው ግዴታ ነው ።

## <u>የተውሂድ ወሳኝነትና ደረጃው፡-</u>

1- ተውሂድ ከእስልምና መሰረቶች የመጀመሪያውን ቦታ የሚይዝ ዋና መሰረት ነው። በመሆኑም አንድ ሰው ወደ እስልምና ሃይማኖት መግባት የሚችለው፡-

ላኢላሀ ኢለላህ ወይም ከአላህ በስተቀር በሀቅ የሚገዙት አምላክ አለመኖሩን ሲመሰክርና አላህን ብቻ መገዛት እንዳለበት አምኖ ሲቀበል ነው ።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

" بُنِيَ الإِسْلاَمُ عَلَى خَمْسٍ: شَهَادَةِ أَنْ لاَ إِلَهَ إِلا اللَّهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللَّهِ، وَإِقَامِ الصَّلاَةِ، وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ، وَالحَجِّ، وَصَوْمِ رَمَضَانَ ".

“ ኢስላም በአምስት ነጥቦች ላይ ተመሰረተ፡- ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ አለመኖሩንና ሙሀመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፤ ሶላትን መስገድ፤ ዘካን መክፈል፤ የተከበረውን የአላህን ቤት ሓጅ (ጉብኝት) ማድረግና የረመዷንን ወር መፆም ናቸው ”ብለዋል።

2- ተውሂድ ከማንኛውም አምልኮ በፊት መታወቅ ያለበትና ወደ እርሱ ጥሪ ሊደረግለት የሚገባው ወሳኝ ነጥብ ነው ።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ሙዓዝ የተባለውን ሱሃቢ "የመን" ወደ ተባለ አገር ላስተማሪነት ሲልኩት፡-

«إِنَّكَ تَأْتِي قَوْمًا مِنْ أَهْلِ الْكِتَابِ، فَادْعُهُمْ إِلَى شَهَادَةِ أَنَّ لا إِلَهَ إِلا اللهُ وَأَنِّي رَسُولُ اللهِ"

*" መጽሐፍ የተሰጣቸውን ሰዎች ታገኛለህ ስለዚህ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት ጌታ አለመኖሩንና እኔ የአላህ መልእክተኛ መሆኔን አስተምራቸው " አሉት።*

3- አንድ አምልኮ ተቀባይነት ያገኝ ዘንድ ተውሂድ ዋና መስፈርትና መሰረት ነው ለምሳሌ፡- ሶላት ያለ ውዱእ ተቀባይነት እንደማያገኝ ሁሉ ማንኛውም አምልኮ ያለ ተውሂድ ተቀባይነት አያገኝም።

4- ተውሂድ በዚችም ሆነ በመጪዋ ዓለም የተቃና እድልና ሰላም ለማግኘት ዋና ምክንያት ነው።

አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

{ الَّذِينَ آمَنُوا وَلَمْ يَلْبِسُوا إِيمَانَهُمْ بِظُلْمٍ أُولَئِكَ لَهُمُ الأَمْنُ وَهُمْ مُهْتَدُونَ } ( الأنعام : 82)

*" እነዚያ ያመኑና እምነታቸውን በበደል ወይም በሽርክ ያልቀላቀሉና ያልበከሉ ሰዎች እነዚያ እነርሱ ሰላምን(መረጋጋትን) ያገኛሉ ። እነሱም ለጥሩ እድል ሁሉ የበቁ ናቸው "* (አል-አንዓም፡82)

እዚህ አንቀፅ ላይ ዙልም ወይም በደል በማለት የተፈለገው በሐዲስ እንደተብራራ ሁሉ ሺርክ ማለት ነው ። ኢብኑ ከሲር የተባሉት ታላቅ አሊም ይህችን አንቀፅ ሲያብራሩ ፡-

*" እነዚያ በአላህ ምንንም ሳያጋሩ አምልኮትን ለእርሱ ብቻ ያደረጉ የቂያማ ቀን ሰላምን ያገኛሉ። በቅረቢቱ ሕይወትና በመጪዋም ዓለም እድለኞች ናቸው"* ብለዋል።

ስለዚህ የተሟላ ተውሂድ ለተሟላ ሰላምና እድል ያበቃል ። ብሎም ያለምንም ቅጣት ጀነትን ለመግባት ያስችላል።

5- በአላህ ማጋራት የመጨረሻ አድሎና በደል ሲሆን አላህን ብቻ መገዛት ደግሞ የመጨረሻ ፍትህ ነው ።

6- ተውሂድ ከእሳት ለመዳንንና ጀነት ለመግባት ዋና ምክንያት ነው። ነብዩ /ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

« مَنْ شَهِدَ أَنْ لاَ إِلَهَ إِلا اللَّهُ وَحْدَهُ لاَ شَرِيكَ لَهُ، وَأَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ، وَأَنَّ عِيسَى عَبْدُ اللَّهِ وَرَسُولُهُ، وَكَلِمَتُهُ أَلْقَاهَا إِلَى مَرْيَمَ وَرُوحٌ مِنْهُ، وَالجَنَّةُ حَقٌّ، وَالنَّارُ حَقٌّ، أَدْخَلَهُ اللَّهُ الجَنَّةَ عَلَى مَا كَانَ مِنَ العَمَلِ»

“ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ አለመኖሩንና ሙሀመድ የአላህ መልእክተኛ እና አገልጋይ መሆናቸውን የመሰከረ፤ እንደዚሁም ኢሳ(ኢየሱስ) የአላህ መልእክተኛና አገልጋይ መሆኑንና አላህ ወደ መርየም ያስተላለፋት በሆነች ቃል የፈጠረውና አላህ ከፈጠራቸው ነፍሶች አንዱ መሆኑን የመሰከረ ፤ ጀነትና እሳትም እውነት መሆናቸውን ያመነና የመሰከረ ሰው ባለው ስራ አላህ ጀነት እንዲገባ ያደርገዋል” ብለዋል።

የአላህ መልእክተኛ/ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሳቸውም፡-

" فَإِنَّ اللَّهَ قَدْ حَرَّمَ عَلَى النَّارِ مَنْ قَالَ: لاَ إِلَهَ إِلا اللَّهُ، يَبْتَغِي بِذَلِكَ وَجْهَ اللَّهِ "

“ የአላህን ፊት ፈልጎ (በፍጹምነት) ላኢላሀ ኢለላህ ወይም ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም ያለ ሰው አላህ ከእሳት እርም ያደርገዋል" ሲሉ ተናግረዋል።

7- ተውሂድ በዚህችም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም ሊያጋጥም ከሚችል አደጋና መከራ ለመዳን ዋና ምክንያት ነው።

8- ተውሂድ ለአላህ ጠላቶችም ሆነ ለወዳጆቹ ዋና መሸሻና መጠጊያ ነው።

- ጠላቶቹ ከዚህች ዓለም ጭንቀትና መከራ እንደሚድኑበት አላህ እንዲህ ሲል ይናገራል፡

{ فَإِذَا رَكِبُوا فِي الْفُلْكِ دَعَوُا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ فَلَمَّا نَجَّاهُمْ إِلَى الْبَرِّ إِذَا هُمْ يُشْرِكُونَ} : العنكبوت: 65)

"በመርከቧም ላይ በተሳፈሩ ጊዜ ፀሎትን ለእርሱ(ለአላህ) ብቻ አድርገው ይለምኑታል። ወደ የብስ በማውጣት ሲያድናቸውም ወዲያውኑ እነርሱ ያጋራሉ"(አል-ዐንከቡት፡65)

- ወዳጆቹ ደግሞ በተውሂዳቸውና በእምነታቸው ምክኒያት በዚህችም ሆነ በመጪዋ ዓለም ሊያጋጥሟቸው ከሚችሉ ችግሮችና ጭንቀቶች ይድኑበታል ።

ለዚህ ነው የአሣው ባለቤት ነቢዩላህ ዩኑስ/ዐለይሂ አሰላሙ/ካጋጠማቸው ጭንቀትና መከራ ለመውጣት አላህን የተማፀኑትና የለመኑት የተውሂድን ቃል በማንሳት የነበረው ።

- ሽርክ ለተለያዩ አደጋዎችና ችግሮች ያጋልጣል። ተውሂድ ከተለያዩ ችግሮች ለመዳን ይረዳል ።

በጠቅላላ ተውሂድ የፉጡራን መሸሻና አስተማማኝ ምሽግ ነው።

9 -ተውሂድ ሰዎችና ጅኖች የተፈጠሩበት ዋና አላማና ግብ ነው።

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል

{ وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالإِنْسَ إِلا لِيَعْبُدُونِ : الذاريات} :56)

" አጋንንትንና ሰዎችንም እኔን ብቻ ሊገዙ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም " (አዛሪያት፡56)

ሰዎች የተፈጠሩት፤ መልዕክተኞች የተላኩት ፤ መጻሕፍት የወረዱት፤ ህግጋት የተደነገጉት አላህ ብቸኛና ፍፁም አምላክ መሆኑ ታውቆ እሱ ብቻ ይመለክ ዘንድ ነው ።

## ላኢላሀ ኢለላህ የሚለው የምስክርነ ቃል ማስረጃና ትርጉም፣

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ شَهِدَ اللَّهُ أَنَّهُ لا إِلَهَ إِلا هُوَ وَالْمَلائِكَةُ وَأُولُو الْعِلْمِ قَائِمًا بِالْقِسْطِ لا إِلَهَ إِلا هُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ } : آل عمران 18)

" በፍትህና በማስተካከል ቋሚ የሆነው አላህ እነሆ ከእርሱ ሌላ በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ መሰከረ። መላእክትና የእውቀት ባለቤቶችም መሰከሩ። አሸናፊና ጥበበኛ ከሆነው ከአላህ ሌላ በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም " (አሊ-ዒምራን፡18)

አላህ በሌላ አንቀጽ ላይ እንዲህ ይላል፡-

(فَاعْلَمْ أَنَّهُ لا إِلَهَ إِلا اللَّهُ ) : محمد 19)

"እነሆ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ አለመኖሩን እወቅ(ተረዳ) "(ሙሐመድ፡19)

### የላኢላሀ ኢለላህ ትክክለኛ ትርጉም፡-

ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም የሚለው ትክክለኛ

የላ-ኢላሀ ኢለላህ ትርጉም ሲሆን የሚከተሉት ትርጉሞች ግን ትክክለኛውን ትርጉም አይወክሉም ፡-

1ኛ-ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም የሚለው ትርጉም ሲሆን ይህ ትርጉም በእውነትም ሆነ በሀሰት የሚመለክ ነገር ሁሉ አላህ ነው ማለትን ስለሚያስረዳ ትክክለኛ የላኢላሀ ኢለላህ ትርጉም አይደለም።

2ኛ- ከአላህ በስተቀር ፈጣሪ የለም የሚለው ትርጉም ደግሞ ከትርጉሞቹ አንዱ ቢሆንም እንኳን የተፈለገው እሱ አይደለም ምክንያቱም ትርጉሙ ይህ ቢሆን ኖሮ በመልእክተኛውና በአጋሪዎች መካከል ጭቅጭቅና አለመግባባት

ባልተፈጠረ ነበር። ምክንያቱም እነርሱ በዚህ ነጥብ ወይም ከአላህ በስተቀር ፈጣሪ የለም በሚለው እውነታ ያምኑ ስለነበሩ ነው ።

3ኛ- ፍርድ የአላህ ብቻ ነው የሚለው ትርጉም ደግሞ ከትርጉሞቹ አንዱ ቢሆንም ነገር ግን እሱ ብቻ በቂ አይደለም።

ምክንያቱም አንድ ሰው  አላህ በፍርድና በውሳኔ ብቸኛ መሆኑን ቢያምንም በሌሎቹ የአምልኮት ዘርፎች ሌላን አካል የሚገዛ ከሆነ ተውሂዱ ሊረጋገጥ ስለማይችል ነው።

**<u>ላኢላህ ኢለላህ የሚለው የምስክርነት ቃል ሁለት ክፍሎች አሉት እነሱም</u> ፦**

1ኛ-"ላኢላሀ" የሚለው ቃል ከአላህ ውጭ የሆነ አካል አምልኮ እንደማይገባው በግልፅ የሚያስረዳ  ሲሆን

2ኛ- "ኢለላህ" የሚለው ቃል ደግሞ አምልኮ ለአላህ ብቻ የሚገባ መሆኑን ያረጋግጣል።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ فَمَنْ يَكْفُرْ بِالطَّاغُوتِ وَيُؤْمِنْ بِاللَّهِ فَقَدِ اسْتَمْسَكَ بِالْعُرْوَةِ الْوُثْقَى لا انْفِصَامَ لَهَا وَاللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ } ( البقرة :256).

“ በጣዖትም የካደና በአላህ ያመነ ሰው የማትበጠስ አስተማማኝ ገመድን በእርግጥ ጨበጠ/ያዘ/ አላህ ሰሚና አዋቂ ነው”(አልበቀረህ: 256)

የካደ የሚለው አምልኮን ከአላህ ውጭ ከሚመለኩ ነገሮች ያነሳና ያስወገደ ማለት ሲሆን ያመነ የሚለው ደግሞ አምልኮን ለአላህ ብቻ ያፀደቀና ያረጋገጠ ማለት  ነው።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَإِذْ قَالَ إِبْرَاهِيمُ لأَبِيهِ وَقَوْمِهِ إِنَّنِي بَرَاءٌ مِمَّا تَعْبُدُونَ (26) إِلا الَّذِي فَطَرَنِي فَإِنَّهُ سَيَهْدِينِ } (27) الزخرف

“ኢብራሂምም ለአባቱና ለወገኖቹ እኔ እናንተ ከምትገዙት ነገር ሁሉ የፀዳሁና የራቅኩ ነኝ ያ የፈጠረኝ ሲቀር እሱም ቀናውን መንገድ በእርግጥ ይመራኛል" ባለጊዜ አስታውስ”(አዙኽሩፍ፡ 27)

## <u>አንድ ሰው ላኢላህ ኢለላህ በሚለው የተውሂድ የምስክርነት ቃል ሊጠቀም የሚችለው ምን ሲያሟላ ነው?</u>

_የቃሉን ትርጉም አውቆ በመልእክቱ ሲሰራ ነው። ትርጉሙና መልእክቱም ከአላህ ውጭ ከሆነ አካል የአምላክነትን ባህሪ አንስቶ ለአላህ ማፅደቅና እርሱን ብቻ  መገዛት ነው።

## <u>ላኢላህ ኢለላህ የሚለው  የምስክርነት ቃል ስምንት መስፈርቶች አሉት። እነሱም፡-</u>

1- ማወቅ፤

2- እርግጠኝነት፤

3- ፍጹምነት፣

4- እውነተኝነት፤

5- መውደድ፤

6- መታዘዝ፣

7- መቀበልና

8- ከአላህ ውጭ በሚመለኩ ነገሮች መካድ ናቸው።

የእነዚህ መስፈርቶች ዝርዝርና ማብራሪያ፡-

1-ማወቅ የሚለው መስፈርት፡- ላኢላሀ ኢለላህ የሚለው የምስክርነት ቃል የሚያስረዳውን የማንሳትና የማፅደቅ(አሉታዊና አዎንታዊን) ትርጉም አውቆ በተግባር ላይ ማዋል ማለት ነው አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ فَاعْلَمْ أَنَّهُ لا إِلَهَ إِلا اللَّهُ } محمد: (19)

"እነሆ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ አለመኖሩን እወቅ"( ሙሐመድ፡19)

2- እርግጠኘነት የሚለው መስፈርት፡- ከአላህ ሌላ በሀቅ የሚገዙት አምላክ የለም የሚለውን የተውሒድን ቃል በእርግጠኘነት መናገር ማለት ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ آمَنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ ثُمَّ لَمْ يَرْتَابُوا وَجَاهَدُوا بِأَمْوَالِهِمْ وَأَنْفُسِهِمْ فِي سَبِيلِ اللَّهِ أُولَئِكَ هُمُ الصَّادِقُونَ} ( الحجرات:15)

" ትክክለኛ አማኞች እነዚያ በአላህ እና በመልእክተኛው ያመኑና ከዚያም በእምነታቸው ያልተጠራጠሩ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ ላይ የሚታገሉ ናቸው። እነዚያ እነርሱ እውነተኛ አማኞች ናቸው" (አል-ሁጁራት፡15)

3-ፍፁምነት የሚለው መስፈርት ሊረጋገጥ የሚችለው የአምልኮ ዓይነቶች በሙሉ ለአላህ ብቻ ሲውሉ ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{وَمَا أُمِرُوا إِلَّا لِيَعْبُدُوا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ حُنَفَاءَ} (البينة :5)

"ቀጥተኞች እና ኃይማኖትን ፍፁም ለአላህ ብቻ አድርገው ሊገዙት እንጂ አልታዘዙም" ( አል-በይነህ: 5)

4- እውነተኘነት ማለት የተውሂድን የምስክርነት ቃል( ላኢላሀ ኢለላህን) በምላሱ ሲናገር በልቡ አምኖ መናገር ማለት ነው።

አላህ እንዲህ ይላል :

{ الم (**1**) أَحَسِبَ النَّاسُ أَنْ يُتْرَكُوا أَنْ يَقُولُوا آمَنَّا وَهُمْ لا يُفْتَنُونَ (**2**) وَلَقَدْ فَتَنَّا الَّذِينَ مِنْ قَبْلِهِمْ فَلَيَعْلَمَنَّ اللَّهُ الَّذِينَ صَدَقُوا وَلَيَعْلَمَنَّ الْكَاذِبِينَ}(العنكبوت :**1-3**).

"ሰዎች ሳይፈተኑ (ሳይሞከሩ) አምነናል በማለታቸው ብቻ የሚተዉ መሰላቸውን? ከእነሱ በፊት የነበሩትን በእርግጥ ፈትነናቸዋል አላህ እነዚያን እውነተኞችንና ሀሰተኞችን ለይቶ ያውቃል" ( አል-ዐንከቡት: 1-3 )።

5- መውደድ የሚለው መስፈርት ላኢላሀ ኢለላህ የሚለውን የምስክርነት ቃል ሲናገር አላህንና መልእክተኛውን፤ የቃሏን መልእክትና ትርጉም በልቡ ወዶ መናገር ማለት ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَمِنَ النَّاسِ مَنْ يَتَّخِذُ مِنْ دُونِ اللَّهِ أَنْدَادًا يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ اللَّهِ وَالَّذِينَ آمَنُوا أَشَدُّ حُبًّا لِلَّهِ } ( البقرة :165)

"ከሰዎችም እንደ አላህ አድርገው የሚወዷቸው የሆኑ ጥዖታትን የሚገዙ አሉ እነዚያ ያመኑትም አላህን ከማንኛውም በላይ ይወዳሉ" (አልበቀረህ- 175)።

6- መታዘዝ የሚለው መስፈርት፡- አላህን ብቻ መገዛትና ለሕጉ ታዛዥ መሆን ማለት ነው።

አላህ እንዲህ ይላል.፡-

{ وَأَنِيبُوا إِلَى رَبِّكُمْ وَأَسْلِمُوا لَهُ } : الزمر: 54)

" ወደ ፈጣሪያችሁም ተመለሱ ለእሱም እጅ ስጡ" ( አዙመር: 54)

7- መቀበል የሚለው መስፈርት፡- የምስክርነት ቃሏንና መልእክቷን ከልቡ አምኖ መቀበል ማለት ነው  ይህም የሚረጋገጠው ከአላህ ውጭ የሚመለኩ ነገሮችን ትቶ  አላህን ብቻ በመገዛት ነው ።

8- ከአላህ ውጭ በሚመለኩ ነገሮች መካድ የሚለው መስፈርት ደግሞ ከአላህ ሌላ የሚመለኩ ነገሮች በሙሉ የውሸት አማልክት መሆናቸውን አውቆና አምኖ እነሱን ከመገዛት መፅዳትና መራቅ ማለት ነው።

አላህ እንዲህ ይላል፦

{ فَمَنْ يَكْفُرْ بِالطَّاغُوتِ وَيُؤْمِنْ بِاللَّهِ فَقَدِ اسْتَمْسَكَ بِالْعُرْوَةِ الْوُثْقَى لا انْفِصَامَ لَهَا وَاللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ } البقرة: 256)

" በጣዖትም የካደና በአላህ ያመነ ለእርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ(ያዘ)። አላህም ሰሚና አዋቂ ነው" (አል-በቀረህ: 256) ።

## ማሳሰቢያ

አንድ ሰው እነኝህን መስፈርቶች ሳያረጋግጥና ሳያሟላ በአንደበቱ ብቻ ላኢላሀ ኢለላህ ማለቱ ተጠቃሚ አያደርገውም።

## ሙሀመድ /ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም/ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን ማመንና መመስከር፦

ይህ ማለት እሳቸው የአላህ ባሪያ መሆናቸውን እና ለሁለት ከባድ ፍጡራን ( ለሰዎችና ለጅኖች) የተላኩ መሆናቸውን ከልብ ማመን እና በአንደበት መመስከር ነው።

አላህ እንዲህ ይላል፦

{ وَاللَّهُ يَعْلَمُ إِنَّكَ لَرَسُولُهُ: المنافقون } (1)

" አላህም አንተ የእርሱ መልእክተኛ መሆንህን ያውቃል"(አል-ሙናፊቁን: 1)

በሌላም አንቀፅ አላህ እንደዚህ ይላል፦

{ لَقَدْ جَاءَكُمْ رَسُولٌ مِنْ أَنْفُسِكُمْ عَزِيزٌ عَلَيْهِ مَا عَنِتُّمْ حَرِيصٌ عَلَيْكُمْ بِالْمُؤْمِنِينَ رَءُوفٌ رَحِيمٌ } ( التوبة: 128)

“ በእርግጥ ከራሳችሁ ጎሳ የሆነ መልእክተኛ መጣላችሁ (ተላከላችሁ) ይህ መልዕክተኛ ችግራችሁ የሚያስጨንቀው ለናንተ መልካምና ጥሩ እድል የሚጥርና የሚጓጓ ለምእምናንም እጅግ በጣም አዛኝና ሩኅሩኅ የሆነ መልዕክተኛ ነው” (አተውበህ- 128)

ይህች የምስክርነት ቃል ሁለት ክፍሎች አሏት እነሱም፡-

እሳቸው የአላህ መልእክተኛ እና ባሪያው መሆናቸውን አምኖ መቀበል ናቸው።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ مُحَمَّدٌ رَسُولُ اللَّهِ: محمد} (29)

“ሙህመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው” ( ሙሐመድ: 29)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَأَنَّهُ لَمَّا قَامَ عَبْدُ اللَّهِ يَدْعُوهُ كَادُوا يَكُونُونَ عَلَيْهِ لِبَدًا } : الجن 19 )

“እነሆ የአላህ ባሪያ (ሙሐመድ አላህን) ለመገዛት በተነሳ ጊዜ (ኢጋንንት)( በመማረክ )በእርሱ ላይ ድርብርቦች ሊሆኑ ቀረቡ” (አል-ጅን፡ 19)

ከዚህ የምንረዳው ዋና ቁም ነገር እሳቸው የማይስተባበሉ መልእክተኛ እና የማይመለኩ የአላህ ባሪያ መሆናቸውን ነው።

እሳቸው የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን ስንመሰክር ወሳኝ የሆኑ አራት ነጥቦችን ማሟላት ይኖርብናል እነሱም፡- 1- የተናገሩትን እውነት ብለን መቀበል።

2- ትእዛዛቸውን ማክበር ።

3- የከለከሉትንና ያስጠነቀቁትን ሙሉ ለሙሉ መራቅና

4-አላህን ስንገዛ በፈጠራና በዘፈቀደ ሳይሆን በእሳሣቸው አስተምህሮት ብቻ በመወሰን መገዛት ናቸው።

## ሽርክ እና ዓይነቶቹ፡-

ሽርክ በቋንቋ ደረጃ ማጋራትና ማወዳደር ማለት ሲሆን ሀይማኖታዊ ትርጉሙ ደግሞ ከአምልኮት ዘርፎች የተወሰነ እንኳን ቢሆን ከአላህ ሌላ ለሆነ አካል አሳልፎ በመስጠት በአላህ ማጋራት ማለት ነው።

እርሱም ከፍተኛውና መለስተኛው ማጋራት ተብሎ በሁለት ይከፈላል ፡-

1- ማንኛውም ከእስልምና ኃይማኖት የሚያስወጣ ወንጀል ሁሉ ከፍተኛው የማጋራት ወንጀል ሲባል ፣

2- ማንኛውም በቃልም ሆነ በተግባር የሚሰራ ወንጀል ማጋራት ወይም ክህደት የሚል ስያሜ ቢሰጠውም ከእስልምና ኃይማኖት የማያስወጣ ከሆነ መለስተኛው የማጋራት ወንጀል ይባላል።

## የትልቁ ማጋራት ዓይነቶች፡-

ትልቁ ማጋራት በአራት መልኩ ሊገለፅ ይችላል እሱም ፡-

1- ከአላህ ሌላ የሆነን አካል በመለመንና በመፀለይ የሚፈፀም የማጋራት ወንጀል ፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ فَإِذَا رَكِبُوا فِي الْفُلْكِ دَعَوُا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ فَلَمَّا نَجَّاهُمْ إِلَى الْبَرِّ إِذَا هُمْ يُشْرِكُونَ : العنكبوت } **(65).**

“በመርከቧም ላይ በተሳፈሩ ጊዜ አላህን ብቻ ይጸልያሉ። ወደ የብስ በማውጣት ሲያድናቸውም ወዲያውኑ እነርሱ ያጋራሉ”(አል-አንከቡት- 65)።

2- በአስተሳሰብ የሚፈፀም የማጋራት ወንጀል ፡-

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ مَنْ كَانَ يُرِيدُ الْحَيَاةَ الدُّنْيَا وَزِينَتَهَا نُوَفِّ إِلَيْهِمْ أَعْمَالَهُمْ فِيهَا وَهُمْ فِيهَا لا يُبْخَسُونَ (15) أُولَئِكَ الَّذِينَ لَيْسَ لَهُمْ فِي الآخِرَةِ إِلا النَّارُ وَحَبِطَ مَا صَنَعُوا فِيهَا وَبَاطِلٌ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ } ( هود:16)

" ቅርቢቱን ሕይወትና ጌጧን የሚሹ ሰዎች የሥራዎቻቸውን (ምንዳ) በእርሷ ውስጥ እንሰጣቸዋለን፡፡ እነሱም በርሷ ውስጥ አይጎድልባቸውም ፤ (15) እነዚያ እነርሱ በመጨረሻይቱ ዓለም ከእሳት በቀር የላቸውም (በቅርቢቱ ዓለም) ይሠሩት የነበሩት በጎ ሥራም ተበላሸ " (ሁድ፡ 16)

3- ከአላህ ውጭ የሆነ አካል አላህ የከለከለውን ሲፈቅድ ወይም የፈቀደውን ሲከለክል አቤት ብሎ በመታዘዝ የሚፈፀም የሽርክ አይነት፡-

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ اتَّخَذُوا أَحْبَارَهُمْ وَرُهْبَانَهُمْ أَرْبَابًا مِنْ دُونِ اللَّهِ وَالْمَسِيحَ ابْنَ مَرْيَمَ وَمَا أُمِرُوا إِلا لِيَعْبُدُوا إِلَهًا وَاحِدًا لا إِلَهَ إِلا هُوَ سُبْحَانَهُ عَمَّا يُشْرِكُونَ } (التوبة:31)

"አላህን ብቻ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሆነው እያለ ሊቃውንቶቻቸውን፤ መነኮሳቶቻቸውንና አልመሲህንም የመርየምን ልጅ ከአላህ ውጭ አማልክት አድርገው ያዙ ። ከእርሱ(ከአላህ) በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም እነሱም ከሚያጋሩት ነገር የፀዳ ነው" (አተውበህ: 31)።

አንቀፁም በአጭሩ እና በቀላሉ ሲተረጎም ለሊቃውንቶችና ለመነኮሳቶች በቀጥታ ባይሰገድ እና ባይፆምም አላህ የከለከለውን ሲፈቅዱ ወይም የፈቀደውን ሲከለክሉ ያለምንም ተቃውሞ አቤት ብሎ መቀበልና መታዘዝ እነሱን እንደመገዛት ይቆጠራል። ነቢዩ /ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም/ ዐዲይ ኢብኑ ሃቲም ለተባለው ሰሀቢይ ይህን አንቀፅ ሲያነቡለት እኛ ሊቃውንቶችን አልተገዛንም ሲላቸው የሰጡት ምላሽ ይህን ነበር ።

4- ከአላህ ውጭ የሆነን አካል እንደ አላህ አድርጎ በመውደድ የሚፈፀም የማጋራት ወንጀል አይነት ፤ አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَمِنَ النَّاسِ مَنْ يَتَّخِذُ مِنْ دُونِ اللَّهِ أَنْدَادًا يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ اللَّهِ }( البقرة:**16**)

“ ከሰዎችም እንደ አላህ የሚወዷቸውን ጣዖታት ከአላህ ሌላ  የሚገዙ አ” አል-በቀረህ: 16)።

## <u>የከፍተኛው ማጋራት ምሣሌዎች፡-</u>

1-ከአላህ ሌላ ለሆነ አካል ቁርባን ማቅረብ፤ መሣልና አላህ እንጂ ማንም መስጠት የማይችለውን ነገር ከአላህ ሌላ ከሆነ አካል መጠየቅ ከፍተኛና ግልፅ የማጋራት ወንጀል ሲሆን ፣

2- አላህ እንጂ ማንም ሊያደርሰው የማይችለውን  ችግር ከአላህ ውጭ  የሆነ አካል  ያደርስብኛል ብሎ መፍራት ደግሞ ከፍተኛና ስውር የማጋራት ወንጀል ይባላል።

## <u>የመለስተኛው ማጋራት ምሣሌዎች፡-</u>

1- ከአላህ ሌላ በሆነ አካል መማል፤ አላህ እና አንተ እያላችሁ፤ እገሌና አላህ ባይኖሩ ኖሮ ማለት እና የመሳሰሉት ግልፅና መለስተኛ ማጋራት ሲሆኑ ለይስሙላ መስራት፤በገድ ማመን እና የመሣሠሉት ደግሞ ስውርና መለስተኛ የማጋራት ወንጀል ናቸው።

## <u>በከፍተኛውና በመለስተኛው የማጋራት ወንጀል  መካከል ያለው ልዩነት፡-</u>

1- ከፍተኛው የማጋራት ወንጀል ከእስልምና ኃይማኖት ሲያስወጣ ፣ መለስተኛው የማጋራት ወንጀል  አለማስወጣቱ፤

2- ከፍተኛው የማጋራት ወንጀል ያለበት ሰው ከዚህ ወንጀሉ ሳይመለስ(ንስሓ ሳያደርግ) ከሞተ በጀሐነም ውስጥ በቋሚነት የሚቀጣ ሲሆን፣ መለስተኛው የማጋራት ወንጀል ያለበት ግን የወንጀሉን ያህል ተቀጥቶ ጀነት የመግባት እድል መኖሩ፤

3- ከፍተኛው የማጋራት ወንጀል መልካም ስራዎችን በሙሉ ሲያወድም፣ መለስተኛው የማጋራት ወንጀል ግን ከእርሱ ጋር ግንኙነት ያለውን ስራ ብቻ ማውደሙና

4- ከፍተኛው የማጋራት ወንጀል ያለበት ግለሰብ ደሙም ሆነ ንብረቱ የተፈቀደ መሆኑ ናቸው።

## የማጋራትን ወንጀል ለመከላከል ጠቃሚ ዱዓ( ፀሎት)፦

አቡሙሳ የተባሉ ታላቅ ሰሀቢ አንድ ቀን የአላህ መልዕክተኛ /ﷺ/ ሲመከሩን ፦

«أَيُّهَا النَّاسُ اتَّقُوا هَذَا الشِّرْكَ؛ فَإِنَّهُ أَخْفَى مِنْ دَبِيبِ النَّمْلِ» . فَقَالَ لَهُ: مَنْ شَاءَ اللَّهُ أَنْ يَقُولَ وَكَيْفَ نَتَّقِيهِ، وَهُوَ أَخْفَى مِنْ دَبِيبِ النَّمْلِ يَا رَسُولَ اللَّهِ؟ قَالَ: قُولُوا: «اللَّهُمَّ إِنَّا نَعُوذُ بِكَ مِنْ أَنْ نُشْرِكَ بِكَ شَيْئًا نَعْلَمُهُ، وَنَسْتَغْفِرُكَ لِمَا لا نَعْلَمُ»

“ እናንተ ሰዎች ሆይ! ይህን የማጋራት ወንጀል ተጠንቀቁት እርሱ ከጉንዳን ኮቴና እንቅስቃሴ ይበልጥ ስውር ነው" ከጉንዳን እንቅስቃሴና ኮቴ ይበልጥ ስውር ከሆነ እንዴት መጠንቀቅ እንችላለን ? ሲሏቸው፡- " አላህ ሆይ! እያወቅን ባንተ ከማጋራት ባንተው እንጠበቃለን ለማናውቀው ደግሞ ምህረትህን እንጠይቃለን በማለት አላህን ለምኑ አሉ”።

## በአላህ የማጋራት ወንጀል አመጣጥ፦

አላህ ብቸኛ ፈጣሪና አምላክ መሆኑን ማመን የሰው ልጆች ጥንታዊና ነባሩ እምነት ነው በአላህ የማጋራት ወንጀል ደግሞ ከግዜ በኋላ የመጣ ጣልቃ ገብ እምነት ነው። ኢብኑ አባስ የተባሉ ታላቅ ሶሀቢ በአደምና በኑህ መካከል አስር ክፍለ-ዘመናት ነበሩ በነዚህ ክፍለ-ዘመናት የነበሩት ሕዝቦች በሙሉ እምነታቸው ተውሂድ (አላህን ብቻ ማምለክ) ነበር ሲሉ ተናግረዋል።

## የማጋራት ወንጀል እንዴት መጣ?

በአላህ የማጋራት ወንጀል ለመጀመሪያ ግዜ በምድር ላይ የተከሰተበት ዋና ምክንያት በአላህ ወዳጆችና በደጋግ ሰዎች ድንበር ማለፍ ነው። ለዚህም አደገኛ ለሆነው ወንጀል የመጀመሪያ ተዋናይና ምክንያት የሆኑት የነቢዩላህ ኑህ ወገኖች ናቸው። ይኸውም የሚወዷቸውና የሚያከብሯቸው የነበሩት ደጋግ ሰዎች ሲሞቱ ለታሳቢነት በሚል በሰይጣን አደገኛ አስተያየት ተነሳስተው ሀውልቶቻቸውን በመስራትና ምስሎቻቸውን በመሳል ድንበር አለፉ። ከዚያም ጊዜው እየረዘመ ሲመጣና ስለነዚህ ደጋግ ሰዎች ማንነት የሚያውቁት ሰዎች ሲጠፉና ሲሞቱ ተተኪው ትውልድ በሰይጣን ግፊትና ተባባሪነት በቀጥታ አመለኳቸው። ከዚያም አላህ ኑህን ወደ ተውሂድ ይጠራቸው ዘንድ ላከላቸው ።

-የሙሳ ወገኖች ጥጃውን(ወይፈኑን) ከአላህ ውጭ አምላክ አድርገው በመያዝ የማጋራት ወንጀልን ለሁለተኛ ጊዜ አደሱት ።

-ክርስቲያኖች ደግሞ በተራቸው የአላህ ባሪያ የሆነውን ኢሳን ወይም ኢየሱስን ወደ ሰማይ ከወጣ በኋላ ለተንኮልና ለማታለል በየኢሱስ አመንኩ ያለ አንድ ጳውሎስ የተባለ ግለሰብ መጥቶ የስላሴንና የመስቀልን እምነት በማስተማር ይህን የማጋራትን ወንጀል እንዲቀጥል አደረገው ።

-አንድ ዐምር ብኑ ሉሀይ የተባለ ግለሰብ ከሻም ሀገር ወደ ሂጃዝ ወይም ዐረብ አገር ጣዖታትን በመውሰድ ሰዎች በትክክለኛው በኢብራሂም ኃይማኖት ፈንታ ጣዖታትን እንዲያመልኩ በማድረግ ይህ የማጋራት ቫይረስ ወደ ዐረብ ሀገራት እንዲተላለፍ አደረገ ።

## በአላህ የማጋራት ወንጀል በነቢዩ ሙሐመድ ሕዝቦች ውስጥ እንዴት ሊከሰት ቻለ?

እንደ ዓመተ-ሒጅራ አቆጣጠር ከአራት መቶ ክፍለ-ዘመን በኋላ የመልእክተኛውን /ﷺ/ ልጅ ፋጢማን እንወዳለን የሚሉ ግለሰቦች በመቃብር ላይ የተለያዩ ቁባዎችን በመስራት የእስልምና ኃይማኖት የማያውቀውን ልደት

ወይም መውሊድ የሚባል ፈጠራን በመፍጠርና በጠቅላላ በሷሊሆች ድንበር በማለፍ ይኸው የማጋራት ወንጀል በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ እንዲስፋፋና እንዲቀጥል አደረጉት ፡፡

## በአላህ ማጋራት የሚያስከትለው መዘዝ፡-

1-በአላህ ማጋራት በተውበት (ንስሓ) እንጂ የማይማር ከባድ ወንጀል ነው

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ إِنَّ اللَّهَ لَا يَغْفِرُ أَنْ يُشْرَكَ بِهِ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَلِكَ لِمَنْ يَشَاءُ وَمَنْ يُشْرِكْ بِاللَّهِ فَقَدِ افْتَرَى إِثْمًا عَظِيمًا} النساء: (**48**)

"አላህ በእርሱ የማጋራትን ወንጀል በፍጹም አይምርም፡፡ ከዚህ ሌላ የሆነን (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል፡፡ በአላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኀጢአት በእርግጥ ቀጠፈ" (አኒሳእ: 48)፡፡

2- ከፍተኛው የማጋራት ወንጀል ከእስልምና ኃይማኖት ያስወጣል፡- አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ فَإِذَا انْسَلَخَ الْأَشْهُرُ الْحُرُمُ فَاقْتُلُوا الْمُشْرِكِينَ حَيْثُ وَجَدْتُمُوهُمْ وَخُذُوهُمْ وَاحْصُرُوهُمْ } (التوبة : **5**)

" የተከበሩት የሓጅ ወራት ሲያልፉ(የሚዋጓችሁን) ጣኦታዊያን በተገኙበት ሥፍራና አጋጣሚ ግደሏቸው፤ ያዟቸውም ከበቧቸውም"(አተውበህ: 5)

3- ከፍተኛው የማጋራት ወንጀል ያለበት ሰው የሚሰራው መልካም ስራ ሁሉ ተቀባይነት አያገኝም የሰራውም መልካም ስራ በአየር ላይ እንደተበተነ አመድ ይሆናል፡-

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَقَدِمْنَا إِلَى مَا عَمِلُوا مِنْ عَمَلٍ فَجَعَلْنَاهُ هَبَاءً مَنْثُورًا } (الفرقان: **23**)

" ወደ ሰሩት ስራም አሰብን እንደተበተነ ገለባም አደረግነው" (አልፉርቃን: 23)

አላህ በሌላም  አንቀፅ  ላይ እንዲህ ይላል፡-

{ وَلَقَدْ أُوحِيَ إِلَيْكَ وَإِلَى الَّذِينَ مِنْ قَبْلِكَ لَئِنْ أَشْرَكْتَ لَيَحْبَطَنَّ عَمَلُكَ وَلَتَكُونَنَّ مِنَ الْخَاسِرِينَ } (الزمر:**65**)

" በእርግጥም ወደ አንተና ካንተ በፊት ወደ ነበሩት ነቢያት ወህይ(ራእይ) ወረደ ካጋራህ በእርግጥ ስራህ ይወድማል ከከሳሪዎችም ትሆናለህ"( አዙመር: 65) ።

4- ከፍተኛው የማጋራት ወንጀል ያለበት ሰው ጀነት የመግባት እድሉ የጨለመና የተቃጠለ ነው የዘላለም መኖሪያውም በጀሀነም ወይም በሲኦል ውስጥ ይሆናል  ። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ إِنَّهُ مَنْ يُشْرِكْ بِاللَّهِ فَقَدْ حَرَّمَ اللَّهُ عَلَيْهِ الْجَنَّةَ وَمَأْوَاهُ النَّارُ وَمَا لِلظَّالِمِينَ مِنْ أَنْصَارٍ } المائدة:**72**) .

" እነሆ በአላህ የሚያጋራ ሰው በእርግጥ አላህ በሱ ላይ ጀነትን እርም አድርጓል መኖሪያውም እሳት ናት። ለግፈኞች(ለአጋሪዎችም) ማንም ከአላህ ቅጣት ሊረዳቸው የሚችል ሀይል የለም " (አልማኢዳ: 72)።

## <u>የእስልምናን እምነት የሚያበላሹ ነገሮች፡-</u>

እስልምናን የሚያበላሹ ብዙ ነገሮች አሉ ይሁን እንጂ በጣም አደገኛ እና ብዙ ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉት በአስር ነጥቦች ይካተታሉ እነሱም፣-

1- ከአላህ ሌላ የሆነን አካል በእርሱ ማጋራት ለምሳሌ ለጅን፤ ለመቃብር እና ለመሳሰሉት የውሸት አማልክቶች ማረድ።

2- ወደ አላህ የሚያማልዱና የሚያቃርቡ ግለሰቦች አሉ ብሎ ማመን። ይህም በዑለሞች መካከል ልዩነት ሳይኖር ከእስልምና ሃይማኖት የሚያስወጣ ወንጀል ነው።

3- የአጋሪዎችን ከሃዲነት መጠራጠር እና ሃይማኖታቸውም ትክክለኛ ነው ብሎ ማመን።

4- ከነብዩ ሙሀመድ /ﷺ/ ኃይማኖት (መንገድ) ውጭ ሌላ የተሻለ ኃይማኖት አለ ብሎ ማመን ወይም ከእሳቸው ፍርድ የበለጠና የተሻለ ፍርድ አለ ብሎ ማመን ፤

5- መልእክተኛው የተላኩበትን ህግና ስርዓት መጥላት ።

6- በአላህ ፤ በመልዕክተኛውና በቁርኣን ማሾፍ። በጠቅላላ በእስልምና ሐይማኖት አስተምህሮ ማሾፍና መሳለቅ፤ አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ قُلْ أَبِاللَّهِ وَآيَاتِهِ وَرَسُولِهِ كُنْتُمْ تَسْتَهْزِئُونَ (65) لا تَعْتَذِرُوا قدكَفَرْتُمْ بَعْدَ إِيمَانِكُمْ } (التوبه:65-66)

“በአላህ፤በአንቀጾቹ እና በመልእክተኛው ታሾፉላችሁን? ምክንያት አታቅርቡ ካመናችሁ በኋላ በእርግጥ ክዳችኋልና በላቸው”( አተውበህ: 65-66) ።

7- ድግምት ማድረግም ሆነ ማስደረግ። እንደዚሁም አንድ ሰው ሌላውን እንዲጠላ ወይም እንዲወድ ማድረግ።

8- ከአጋሪዎች ጋር በመተባበርና በመወገን ሙስሊሞችን መውጋት፤ አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَمَنْ يَتَوَلَّهُمْ مِنْكُمْ فَإِنَّهُ مِنْهُمْ إِنَّ اللَّهَ لا يَهْدِي الْقَوْمَ الظَّالِمِينَ} ( المائده: 51).

“ከእናንተ እነሱን (አጋሪዎችን) ወዳጅ አድርጎ የሚይዝ እሱ ከእነሱ ይመደባል ። አላህ አጋሪ ሰዎችን አይመራም ” (አል-ማኢዳ: 51)።

9- ከእስልምና ኃይማኖት ውጭ ሌላ ትክክለኛና የተሻለ ኃይማኖት አለ ብሎ ማመን፤ አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَمَنْ يَبْتَغِ غَيْرَ الْإِسْلَامِ دِينًا فَلَنْ يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِي الآخِرَةِ مِنَ الْخَاسِرِينَ } :

(آل عمران: **85**).

" ከእስልምና ኃይማኖት ውጭ ሌላ ኃይማኖትን የሚሻ ከእሱ ተቀባይነት አያገኝም እሱም በመጪዋ ዓለም ከከሳሪዎች ይሆናል"(ኣሊዒምራን: 85)።

10- የእስልምናን ኃይማኖት ተምሮ በስራ ላይ ማዋል  ሲገባው ቸል ማለት አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنْ ذُكِّرَ بِآيَاتِ رَبِّهِ ثُمَّ أَعْرَضَ عَنْهَا إِنَّا مِنَ الْمُجْرِمِينَ مُنْتَقِمُونَ }

(السجدة **22**).

" በአላህ አንቀጾች ተመክሮ እርሷን ቸል ያለ ወይም ዘወር ካለ ሰው የበለጠ በደለኛ የለም  እኛ ጠማሞችን ተበቃዮች ነን " (አስ-ሰጅዳ: 22)

## ማሳሰቢያ፡-

1- እነዚህን የተጠቀሱትን የኢስላም አፍራሾች ተገዶ ካልሆነ በስተቀር ሆን ብሎም ሆነ በግደለሽነት መፈፀም ልዩነት የለውም።

2- እነኝህ አፍራሾች በጣም አደገኛና ብዙ ግዜ የሚከሰቱ ስለሆኑ ማንኛውም ሙስሊም አውቆ ሊጠነቀቃቸው ይገባል ።

## ጣዖት፡-

ከአላህ ውጭ የሆነን አካል በመገዛት ፤በመታዘዝ እና በመከተል ድንበር የታለፈበት ነገር ሁሉ ጣዖት ይባላል።

## በጣዖት መካድ ግዴታ ስለ-መሆኑ፡-

በሰው ልጆች ላይ የተጣለው የመጀመሪያው ግዴታ በጣዖት መካድ እና በአላህ ማመን ነው ። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِي كُلِّ أُمَّةٍ رَسُولا أَنِ اعْبُدُوا اللَّهَ وَاجْتَنِبُوا الطَّاغُوت}( النحل:**37** ).

“ በማንኛውም ሕዝብ ውስጥ አላህን ተገዙ ጣዖትንም ራቁ በማለት የሚያስተምር መልዕክተኛን በእርግጥ ልከናል”( አል-ነህል: 36)

## በጣዖት መካድ፡-

በጣዖት መካድ ማለት፡- ከአላህ ውጭ የሚገዙት ነገር ሁሉ ከንቱ መሆኑን አምኖ መተውና ጣዖት አምላኪዎች ከሃዲያን መሆናቸውን አውቆ ከእነሱም ሆነ ከተግባራቸው ነፃ መሆንና መራቅ ማለት ነው።

## የጣዖት አለቃዎች፡-

1- የአላህ እርግማን የተረጋገጠበት ሰይጣን፤

2- ከአላህ ውጭ በፍቃዱ የሚመለክ፤

3- ሰዎች እሱን ያመልኩት ዘንድ ጥሪ የሚያደርግ እና

4- የሩቅ ወይም የሚስጥር እውቀት አውቃለሁ የሚል ሰው ናቸው።

## ማንኛውም ሰው በሕይወት እያለ ማወቅ ያለበትና በቀብር ውስጥ ለፈተና የሚቀርቡ ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉ እነሱም፡-

1ኛ- ስለ ፈጣሪው ማወቅ፤

2ኛ- ስለነቢዩ ሙሀመድ /ﷺ/ መልእክተኝነት ማወቅና

3ኛ- የእስልምና ኃይማኖትን በሚገባ መረዳት ናቸው።

የእነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች ዝርዝርና ማብራሪያ፡-

* የመጀመሪያው መሰረታዊ ጥያቄ ስለፈጣሪ ማወቅና መረዳት ሲሆን በውስጡ የሚከተሉትን ወሳኝ ነጥቦች ያካትታል። እነሱም፡-

1- ያ እኛንም ሆነ ዓለማትን የፈጠረና በተለያዩ ፀጋዎቹ የሚንከባከበን አላህ ብቻ መሆኑን ማወቅ።

2- ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ አለመኖሩን ማወቅና ማመን።

3- ፈጣሪያችንን በተለያዩ ምልክቶች እና ታላላቅ በሆኑ ፍጥረታት ማወቅ እንደሚቻል መገንዘብ። ለምሣሌ የእሱን ፈጣሪነት እና ብቸኛ አምላክ መሆኑን ከሚጠቁሙ ምልክቶች፡-

ሀ- ሁለት ተፈራራቂ የሆኑ ሌሊትና ቀን፤

ለ- ፀሐይና ጨረቃ፤

መ- ሰባት ሰማያትና ሰባት ምድሮች፤ እንደዚሁም በውስጣቸውና በመካከላቸው ያለ ነገር ሁሉ አላህ ብቸኛ ፈጣሪና አምላክ መሆኑን ይጠቁማል።

*-ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ ስለ እስልምና ሃይማኖት ማወቅና መረዳት ሲሆን በውስጡ ሶስት ነጥቦችን ያካትታል።

1- አላህ የወደደውና የመረጠው ሃይማኖት እስልምና ብቻ መሆኑን ማወቅ፣

2- ኢስላም ማለት ለአላህ እጅ መስጠት፤ ለእሱም መታዘዝ፤ ከሽርክና ከሽርክ ባለቤቶች ነፃ መሆንና መራቅ ነው።

3- ኢስላም፤ ኢማን እና ኢህሳን የሀይማኖቱ ደረጃዎች መሆናቸውን ማወቅና መረዳት ናቸው።

*- ሦስተኛው መሰረታዊ ጥያቄ ስለነቢዩ ሙሀመድ /ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለመ/ ማወቅ ሲሆን በውስጡ ብዙ ወሳኝ ነጥቦች ይካተታሉ፡-

፣- ስማቸውን ከነዘር ሀረጋቸው ማወቅ ሲሆን ስማቸውም፡- ሙሐመድ ኢብኑ ዐብዱላህ ኢብኑ አብዱል ሙጦሊብ ኢብኑ ሃሺም ይባላል። ሐሺም የቁረይሾች ተወላጅ ነው። ቁረይሾች ደግሞ የዐረብ ተወላጆች ናቸው ዐረቦች ከኢስማዒል የዘር ሀረግ ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ ናቸው።

2- የእድሜ ክልላቸው ስልሳ ሦስት አመታት መሆኑንና አርባዎቹን ከመላካቸው በፊት ሲያሳልፏቸው ሃያ ሶስቶቹን ደግሞ ነቢይና መልእክተኛ ሆነው እንዳሳለፏቸው ማወቅ፤

3- አንብብ በመባል የነቢይነትን መኣረግ ሲያገኙ ተከናናቢው ሆይ! .በሚለው ደግሞ መልእክተኛ መሆናቸው እንደታወጀ ማወቅ፤

4 -የትውልድ አገራቸው መካ ሲሆን የተሰደዱበት ሀገር ደግሞ መዲና መሆኑን ማወቅ፤

5 -የዳዕዋ( የጥሪ) ዋና ርእሳቸው ከሽርክ ማስጠንቀቅና ወደ ተውሂድ ጥሪ ማድረግ መሆኑን ማወቅ ናቸው።

## ክህደት፡-

ክህደት ማለት የኢስላም ተቃራኒ ሲሆን እሱም ከፍተኛውና መለስተኛው ክህደት ተብሎ በሁለት ይከፈላል፤

ከፍተኛው ክህደት የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል።

፣- ከአላህ የመጣውን እውነት በማስተባበል የሚፈፀም የክህደት አይነት ። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ افْتَرَى عَلَى اللَّهِ كَذِبًا أَوْ كَذَّبَ بِالْحَقِّ لَمَّا جَاءَهُ أَلَيْسَ فِي جَهَنَّمَ مَثْوًى لِلْكَافِرِينَ}( العنكبوت: **68**).

" በአላህ ላይ ውሸትን ከቀጠፈ ወይም እውነቱ ሲመጣለት ካስተባበለ ሰው የበለጠ በደለኛ የለም። በገሀነም ውስጥ ለከሃዲያን መኖሪያ ተዘጋጅቷል" (አል-ዐንከቡት: 78)።

2- ከአላህ የመጣው መመሪያ እውነት መሆኑን እያወቀ በኩራትና ሀቅን ባለመቀበል የሚፈፀም የክህደት አይነት።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَإِذْ قُلْنَا لِلْمَلائِكَةِ اسْجُدُوا لآدَمَ فَسَجَدُوا إِلا إِبْلِيسَ أَبَى وَاسْتَكْبَرَ وَكَانَ مِنَ الْكَافِرِينَ } ( البقرة: **34**).

" ለመላእክትም ለአደም ስገዱ ባልን ግዜ ወዲያውኑ ሰገዱ። ዲያቢሎስ ግን እምቢ አለ ኮራም ከከሃዲያንም ሆነ " (አበቀረህ: 34)።

3- ከእውነት በመዞርና ቸል በማለት የሚፈፀም የክህደት አይነት። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَالَّذِينَ كَفَرُوا عَمَّا أُنْذِرُوا مُعْرِضُونَ }( الأحقاف: **3**) .

" እነዚያ የካዱት ሰዎች ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው ነገር ቸል ይላሉ"(አል-አህቃፍ: 3)

4- በመጪው ዓለም መጠራጠር ለምሳሌ፡- ከሞት በኋላ በመነሳት፤ ጀነትና እሳት የሚባሉ ሁለት ቋሚ አገሮች በመኖራቸውና በመሳሰሉት የአኺራ ጉዳዮች ላይ በመጠራጠር የሚፈጸም ክህደት ነው።

5- በንፍቅና ምክንያት የሚመጣ የክህደት አይነት ። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ ذَلِكَ بِأَنَّهُمْ آمَنُوا ثُمَّ كَفَرُوا فَطُبِعَ عَلَى قُلُوبِهِمْ فَهُمْ لا يَفْقَهُونَ } (المنافقون: **3**).

“ እነሱ ካመኑ በኋላ በመካዳቸው በልቦቻቸው ላይ ታሸገ ስለዚህ እነሱ የሚሰሙትን ምክር መረዳት አይችሉም”(አል-ሙናፊቁን: 3)።

## መለስተኛው ክህደት፡-

ማንኛውም ወንጀል በቁርኣንና በሐዲስ ክህደት የሚል ስያሜ ከተሰጠው እና እንደ ከፍተኛው ክህደት ከእስልምና ሃይማኖት የማያስወጣ ከሆነ መለስተኛው ክህደት ይባላል። እሱም ተውበት የሚያሻው ታላቅ ወንጀል ነው። ምሳሌዎቹም፡-

1- አላህም ሆነ ሰዎች በዋሉለት ውለታ ማመስገን ሲገባው መካድ።

2- አንድ ሙስሊም ሌላ ሙስሊም ወንድሙን መግደል።

የአላህ መልእክተኛ/ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

«سِبَابُ المُسْلِمِ فُسُوقٌ، وَقِتَالُهُ كُفْرٌ» .

“ አንድን ሙስሊም መሳደብ አመጽ ሲሆን መግደሉ ደግሞ ክህደት ነው ” ብለዋል።

3- የሰዎችን የዘር ሀረግ ማንቋሸሽና ማነወር፤

4- በሞተ ሰው ላይ ሙሾ መደርደርና ጮሆ ማልቀስ። የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

" اثْنَتَانِ فِي النَّاسِ هُمَا بِهِمْ كُفْرٌ: الطَّعْنُ فِي النَّسَبِ وَالنِّيَاحَةُ عَلَى الْمَيِّتِ ".

“ ሁለት ነገሮች በሰዎች ዘንድ ክህደት ናቸው የሰዎችን የዘር ሀረግ ማጉደፍና በሞተ ሰው ላይ ሙሾ መደርደር ወይም ጮሆ ማልቀስ” ብለዋል።

## ንፍቅና/አስመሳይነት/፡-

በእንቅስቃሴውና በተግባሩ ሙስሊሞችን መስሎ በልቡ ውስጥ ክህደትን ማሳደር ንፍቅና ይባላል።

ንፍቅና በሁለት ይከፈላል እነሱም፡-

1ኛ- ከፍተኛና እምነታዊ ንፍቅና፤

2ኛ- መለስተኛና ተግባራዊ ንፍቅና ናቸው።

እምነታዊ ንፍቅና ያለበት ግለሰብ ሳይቶብት በንፍቅናው ላይ እያለ ከሞተ የመጨረሻ አዘቅጥ በሆነው የጀሐነም ክፍል እንዲቀጣ ይደረጋል። ይህም እምነት ስድስት መገለጫዎች አሉት። እነሱም፡-

1- መልእክተኛውን ማስተባበል፤

2- ወይም መልእክተኛው ያመጡትን መመሪያ ማስተባበል፣

3- ወይም መልእክተኛውን መጥላት፤

4- ወይም መልእክተኛው ያመጡትን ህግና ስርዓት መጥላት፣

5- ወይም የእስልምና ሃይማኖት የበታች ሲሆን እና ሲረገጥ መደሰትና

6- ኢስላም የበላይነት ሲያገኝ ቅር መሰኘት ናቸው።

ተግባራዊ ንፍቅና ማለት በአላህ ላይ ያለው እምነት በልቡ ውስጥ እያለ የሙናፊቆችን ተግባር ማከናወን ነው። እሱም ከሃይማኖት ባያስወጣም ወንጀልነቱ ከታላላቅ ወንጀሎች ይቆጠራል። ባለቤቱም የእምነትና የንፍቅና ባህሪያትን አስተናጋጅ ይባላል። የሙናፊቆችንም ተግባር ባበዛ ቁጥር ሙናፍቅነቱ እያመዘነ እና ኢማኑ እየተዳከመ ይመጣል። ከዚያም የለየለት ሙናፊቅ ሊሆን ይችላል።

የመለስተኛው ንፍቅና ምሳሌዎች፡-

1- ሲናገር መዋሸት፤

2- ቀጠሮን አለማክበር፣

3- የተሰጠውን አደራ መካድ፤

4- ሲከራከር በውሸት ማሸነፍ(መርታት)፤

5- ቃልኪዳኑን ማፍረስ፤

6- ወደ መስጂድ ሄዶ በህብረት(በጀማዓ) አለመስገድ እና መልካም ስራዎችን ለእዩልኝ መስራት ናቸው ።

## ወላእና በራእ (መውደድና መጥላት) በኢስላም ፡-

ወላእ በቋንቋ ደረጃ መውደድ ማለት ሲሆን በራእ የሚለው ደግሞ መቁረጥና መራቅ ማለት ነው።

የወላእ ሃይማኖታዊ ትርጉም ፡- ሙስሊሞችን መውደድ፤ መርዳት፤ ማክበርና ከነሱ ጋር መቀራረብ ሲሆን በራእ ደግሞ ከሃዲያንን መጥላትና ከነሱ መራቅ  በሃይማኖት ጉዳይም  ከእነሱ ጋር አለመተባበር ማለት ነው።

### የመውደድና የመጥላት ወሳኝነት፡-

1-ከእስላማዊ እምነት መሰረቶች አንዱ መሆኑ፤

2- አስተማማኝ የእምነት ገመድ መሆኑ፤

3- የነቢዩ ኢብራሂምና የነቢዩ ሙሀመድ /ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም/ መንገድና እምነት መሆኑ ናቸው።

## ከሃዲያንን መውደድ በሁለት ይከፈላል፡-

አንደኛው- እነሱን መውደድና በኃይማኖታቸው ጉዳይ መተባበር ሲሆን

ሁለተኛው - ትብብር የሌለው ውዴታ ነው።

ምሣሌዎቹም፡-

1-ማጋራትንና ክህደትን መውደድ፤

2- አጋሪንና ከሃዲያንን መውደድ፤

3- ከከሃዲያን ጋር ወግኖ አማኞችን መውጋትና የመሳሰሉት ናቸው።

ይህ የውዴታ ክፍል ከኃይማኖት የሚያስወጣ ትልቅ ክህደት ነው።

## መውደድ፡-

ከሃዲያንና አጋሪዎችን ለግል ጥቅም ብሎ መውደድና ወዳጅ አድርጎ መያዝ የተከለከለና ከታላላቅ ወንጀሎች የሚመደብ ተግባር ነው።

ከሃዲያንን የመውደድ ምልክቶች፤-

1- በአለባበስና በአነጋገር እነሱን ለመምሰል መሞከር፤

2- ለመዝናናት እና ለመደሰት ብሎ ወደ እነሱ ሀገር መሄድ፤

3- ለሃይማኖቱ ሲል ወደ እስላም ሀገር መሄድ ሲገባው ያለ ምንም ችግር እና ምክንያት በሀገራቸው መኖርን መምረጥ፤

4- በእነሱ አቆጣጠር መቁጠር በተለይም ዓመት ባዓላቸውን የሚገልጽ በሆነው እንደ-ልደት አይነት፤

5-በባዓላቸው መገኘትና መሳተፍ ወይም ለባዓሉ ዝግጅት ትብብር ማድረግና እንኳን ለባዓሉ አደረሳችሁ ማለት፤

6 ከእስልምና ኃይማኖት ጋር የማይጣጣም በሆነው ስማቸው መጠራትና የመሳሰሉት ናቸው።

ከመውደድና ከመጥላት አንፃር ሰዎች በሶስት ይከፈላሉ።

1- ያለምንም ጥላቻ በንፁህ ልቦና የሚዎደዱ ሰዎች አሉ እነሱም ንፁሃን አማኞች ናቸው።

2- ፍፁም የማይወደዱ ብሎም ጠላት ተደርገው የሚያዙ አሉ እነሱም የለየላቸው ከሃዲያን ናቸው።

3- በአንድ በኩል የሚወደዱና በሌላ በኩል ደግሞ የሚጠሉ አሉ እነሱም ከሽርክ በታች ያሉ ወንጀሎችን የሚፈፅሙ አማኞች ናቸው እነዚህ ሰዎች ባላቸው መሰረታዊ እምነትና በሚሰሩት መልካም ሥራቸው ይወደዳሉ በሚፈፅሙት ወንጀል መጠን ደግሞ ይጠላሉ።

## አል -ኢስላም ወይም እስልምና፡-

ኢስላም ማለት ለአላህ ብቻ ታዛዥ መሆን፤ ለሱም እጅ መስጠት፤ ከማጋራት እና ከአጋሪዎች ነፃ መሆን ማለት ነው።

## የኢስላም አጠቃላይና ልዩ ትርጉም፡-

አላህ መልእክተኞችን ከላከበት ጊዜና ወቅት ጀምሮ እስከ ቂያማ ቀን ድረስ እርሱ ባወጣው ህግና ስርዓት መሰረት እሱን ብቻ መገዛት የኢስላም አጠቃላይና ሰፊ ትርጉም ሲሆን ነቢዩ ሙሀመድ /ሶ.ዐ.ወ/ በተላኩበት ህግና ስርዓት ብቻ በመወሰን አላህን መገዛት ደግሞ የኢስላም ልዩ ትርጉም ይሆናል።

## የእስልምና መሰረቶች፡-

ኢስላም አምስት መሰረቶች አሉት እነሱም፡-

1- ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ አለመኖሩንና ሙሀመድ የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን መመስከር፤

2- ሶላትን መስገድ፤

3- ዘካን መስጠት፤

4- የረመዷንን ወር መፆምና

.5- የቻለ ሰው የአላህን ቤት በእድሜው አንድ ግዜ ሐጅ ( ጉብኙት) ማድረግ ናቸው።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

" بُنِيَ الإِسْلاَمُ عَلَى خَمْسٍ: شَهَادَةِ أَنْ لاَ إِلَهَ إِلا اللَّهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللَّهِ، وَإِقَامِ الصَّلاَةِ، وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ، وَالحَجِّ، وَصَوْمِ رَمَضَانَ "

“ኢስላም በአምስት ነገሮች ላይ ተመሰረተ፡-

ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ አለመኖሩንና ሙሀመድ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን መመስከር፤ ሶላትን መስገድ፤ ዘካን መስጠት፤ ሐጅ ማድረግና የረመዷንን ወር መፆም ” ብለዋል።

እነኚህ የእስልምና መሰረቶች በሁለት ይከፈላሉ፡-

አንደኛው ክፍል ሁለት ዋናዋና ነጥቦችን ያካትታል እነሱም፡-

1 - ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ አለመኖሩንና ሙሀመድ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን መመስከር፤

2- አምስት ወቅት ሶላቶችን መስገድ ናቸው። እነዚህ ሁለት ነገሮች የእስልምና ኃይማኖት ዋና መሰረታዊ ነጥቦች ስለሆኑ ያለነሱ አንድ ሰው ሙስሊም ሊባል አይችልም ።

ሁለተኛው ክፍል ሦስት ነገሮችን ያካትታል እነሱም፡-

1- ዘካን መስጠት፤

2- የረመዷንን ወር መፆም፣

3- የቻለ ሰው የአላህን ቤት ጉብኝት ማድረግ ናቸው።

እነዚህ ሦስት ነገሮች ደግሞ እስልምናን የሚያሟሉ ነጥቦች ናቸው።

## የኢማን ትርጉም፡-

ኢማን በቋንቋ ደረጃ እውነት ማለትና መናገር ሲሆን ኃይማኖታዊ ትርጉሙ ደግሞ፡-

1- በልብ ማመን፤

2- በምላስ መናገርና

3- በአካል መተግበር ነው።

ኢማን አላህን በመገዛት ይጨምራል እርሱን በማመጽ ይቀንሳል።

## የእምነት ማዕዘናት

እምነት ስድስት ክፍሎች ወይም ማዕዘናት አሉት እነሱም፡-

1_ በአላህ ማመን፤

2- በመላእክት ማመን፤

3- በመፅሐፍት ማመን፤

4- በመልእክተኞች ማመን፤

5- በመጨረሻው ቀን ማመንና

6- ማንኛውም ነገር ጥሩም ሆነ ክፉ በአላህ ውሳኔ እንደሚፈፀም ማመን ናቸው።

**<u>በአላህ ማመን የሚለው አራት ዋና ዋና ነጥቦችን ያካትታል እነሱም፡-</u>**

1- አላህ መኖሩን ማመን፣

2- አላህ የዓለማት ፈጣሪና አስገኝ መሆኑን ማመን፣

3- ከእርሱ ውጭ በሀቅ የሚገዙት አምላክ አለመኖሩን ማወቅና ማመን፣

4- በስሞቹና በባህርያቱ ማመን ናቸው።

**<u>በመላዕክት ማመን የሚለው አራት ነጥቦችን ያካትታል እነሱም ፡-</u>**

1- አላህ ከብርሃን የፈጠራቸውና እሱን የማይወነጅሉ ቀናኢ አገልጋዮች መሆናቸውን ማወቅና ማመን ፤

2- ከእነሱ ውስጥ በስም የተጠቀሱትን ከነስሞቻቸው ማወቅና ማመን፣

3- ከሰዎች የተለዩ ባህርያት እንዳሏቸው ማወቅና ማመን፤

4- በስራ ድርሻቸው የታወቁትን ከነስራ ድርሻቸው ማወቅና ማመን ናቸው።

**<u>በመጻሕፍት ማመን በሚለው ስር አራት ነጥቦች ይካተታሉ እነሱም፡-</u>**

1- የአላህ ቃልና ከእርሱ የወረዱ መሆናቸውን ማመን፤

2- በስማቸው የታወቁትን ለምሣሌ ፡- እንደ ቁርዓን ፤ ተውራት(ኦሪት) ፤ ኢንጂል(ወንጌል) እና ዘቡር(መዝሙር) ያሉትን ከነስሞቻቸው ማወቅና ማመን፤

3- ቁርዓን የተናገረው እውነት መሆኑን ማመን እና ቀደምት ሰማያዊ መፃሕፍት የተናገሩትም የተዛባና የተበረዘ ካልሆነ በስተቀር እውነት ብሎ ማመንና መቀበል

4 -ቀደምት ሰማያዊ መጻሕፍት በሙሉ በቁርኣን መሻራቸውን አምኖ መቀበል ናቸው።

**<u>በአላህ መልእክተኞች ማመን በሚለው ስር አምስት ነጥቦችን እናገኛለን</u>፡-**

1- አላህ ከሰዎች መካከል መርጦና አብልጦ ሰዎችን ያስተምሩ ዘንድ የላካቸው መሆኑን በእርግጠኝነት ማመን፤

2- ከእነሱ በአንዱ መልእክተኛ መካድ በሁሉም እንደመካድ መሆኑን አውቆ በሁሉም መልእክተኞች ማመን፤

3-ከእነሱ በስሞቻቸው የተጠቀሱትን ለምሳሌ ፡- ሙሀመድ ፤ ኢብራሂም ፤ ሙሳ፤ዒሳ፤ኑህ እና በመሳሰሉት ከነስሞቻቸው አውቆ ማመን፤

4- እነሱ የተናገሩትን እውነት ነው ብሎ ማመንና መቀበል፤

5- በጠቅላላ ለሰዎችና ለአጋንንት በተላኩትና የነቢያት መጨረሻና መደምደሚያ በሆኑት መልእክተኛ- በነቢዩ ሙሀመድ /ﷺ/ ህግና ስርዓት መሰረት አላህን መገዛት ናቸው።

**<u>በመጨረሻው ዕለት ማመን አራት ነገሮችን ያካትታል</u>፡-**

1- ከሞት በኋላ መነሳት የማይቀር መሆኑን ማመን፣

2- በዚች ዓለም በሰሩት ስራ በትንሣኤ ቀን መጠየቅና የስራ ውጤት እንደሚሰጥ ማመን፣

3- ጀነት እና እሳት የሚባሉ ሁለት ቋሚ አገሮች መኖራቸውን ማመን ፣

4- ከሞት በኋላ በሚያጋጥሙ ነገሮች ለምሳሌ፡- በቀብር ውስጥ መጠየቅ ፤ መቀጣት፤ መጠቀምና መደሰት መኖሩን ማመን ናቸው።

**<u>በቀደር ማመን፡-</u>**

በአላህ ውሳኔ ማመን በአራት ነገሮች ማመንን ያጠቃልላል። እነሱም፡-

1- አላህ በጥቅልም ሆነ በዝርዝር ሁሉን ነገር የሚያውቅ መሆኑን ማወቅና ማመን፣

2- አላህ ሁሉን ነገር በተከበረው ሰሌዳ ላይ ቀደም ሲል እንደፃፈውና እንዳ ሰፈረው ማመን፤

3- ማንኛውም ግኝት በአላህ ውሳኔ እና ፍቃድ እንጂ ሊገኝ እንደማይችል ማመን፣

4- ማንኛውም ግኝት በአካሉ፤ በባህሪውና በእንቅስቃሴው የአላህ ፍጡር መሆኑን ማመን ናቸው።

**<u>የእነዚህ ስድስት እምነቶች ማስረጃ፡-</u>**

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ لَيْسَ الْبِرَّ أَنْ تُوَلُّوا وُجُوهَكُمْ قِبَلَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَلَكِنَّ الْبِرَّ مَنْ آمَنَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الآخِرِ وَالْمَلائِكَةِ وَالْكِتَابِ وَالنَّبِيِّينَ }(البقرة:177) .

"ፊቶቻችሁን ወደ ምስራቅና ምእራብ አቅጣጫ ማዞራችሁ መልካም ስራ አይደለም ነገር ግን ትክክለኛ መልካም ስራ የሚባለው በአላህ፤ በመጨረሻው እለት፤ በመላእክት፤ በመፃሕፍትና በነቢያት ያመነ ብቻ ነ" (አል-በቀራህ: 177) ።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{إِنَّا كُلَّ شَيْءٍ خَلَقْنَاهُ بِقَدَرٍ} (القمر: 49) .

"እኛ ማንኛውንም ነገር በውሳኔ/በልክ/ ፈጠር ነው" (አል-ቀመር: 49)

-የአላህ መልክተኛ /ﷺ/ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ጅብሪል የተባለው መልእክ ስለ እምነት አስረዳኝ ሲላቸው፡-

«أَنْ تُؤْمِنَ بِاللهِ، وَمَلَائِكَتِهِ، وَكُتُبِهِ، وَرُسُلِهِ، وَالْيَوْمِ الآخِرِ، وَتُؤْمِنَ بِالْقَدَرِ خَيْرِهِ وَشَرِّهِ»

"በአላህ፤ በመላእክት፤ በመጻሕፍት፤ በነቢያትና ደግም ሆነ ክፉ በአላህ ውሳኔ እንደሚፈፀም ማመን ነው" አሉት።

## በጎ ስራ፡-

በጎ ስራ ማለት በቋንቋ ደረጃ የማስቀየም ተቃራኒ ሲሆን ኃይማኖታዊ ትርጉሙ ደግሞ በገሀድም ሆነ በሚስጥር አላህን መፍራት ለሚለው ያገለግላል።

እርሱም አንድ ማዕዘን አለው እሱም አላህን ልክ እንደሚያይ ሆኖ መገዛት ይህም ካልተቻለ አላህ እንደሚያየውና እንደሚቆጣጠረው አውቆ መገዛት ማለት ነው።

## በጎ ስራ ሁለት ክፍሎች አሉት እነሱም፡-

1- አላህን በሚገባ መገዛት ሲሆን ይህም ሁለት ደረጃዎች አሉት። እነሱም፡-

አንደኛ- አላህን ልክ እንደሚያየው ሆኖ መገዛት ይህም ከሁለቱ ደረጃዎች ከፍተኛው ሲሆን ፣

ሁለተኛ- አላህ እንደሚያየውና እንደሚቆጣጠረው አምኖ መገዛት ናቸው።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ጅብሪል የተባለው መልኣክ ስለ በጎ ስራ ንገረኝ ሲላቸው፡-

«أَنْ تَعْبُدَ اللَّهَ كَأَنَّكَ تَرَاهُ، فَإِنْ لَمْ تَكُنْ تَرَاهُ فَإِنَّهُ يَرَاكَ»

"አላህን እንደምታየው ሆነህ መገዛት አንተ የምታየው ባትሆን እሱ ያይሃልና" አሉት።

2- ለፍጡር በጎ መዋል ይህም በአራት ነገሮች ይገለፃል። እነሱም፡-

በገንዘቡ፤ በእውቀቱ ፤በአካሉና በክብሩ ለሰዎች በጎ መዋል ናቸው።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ إِنَّ اللَّهَ مَعَ الَّذِينَ اتَّقَوْا وَالَّذِينَ هُمْ مُحْسِنُونَ } (النحل : **128**).

"አላህ በእርዳታውና በእንክብካቤው ከነዚያ እሱን ከሚፈሩትና ከበጎ አድራጊዎች ጋር ነው " (አነሕል: 128)።

* - <u>ኢስላም፤ኢማን እና ኢህሳን ያላቸው ግንኙነት</u>፡-

እነዚህ ሶስት ቃላት በጣምራ ሲጠቀሱ የተለያየ ትርጉም አላቸው ለምሳሌ፡-

1- ኢስላም የሚለው በገሃድ ለሚሰሩ ነገሮች ሲያገለግል፤

2- ኢማን የሚለው ደግሞ ህዋሳት ሊደርስባቸው በማይችሉ ሩቅና ሚስጥር ነገሮች ማመን የሚለውን ያስረዳል፣

3- ኢህሳን የሚለው ደግሞ ከኃይማኖት ደረጃዎች ከፍተኛውን ክፍል ይሸፍናል ።

እነዚህ ሦስት ቃላት በተናጠል ሲነገሩ ደግሞ አንዱ በሌላው ስር ይጠቃለላል ለምሳሌ፡-

- ኢስላም የሚለው ብቻውን ከተጠቀሰ በውስጡ ኢማንን ሲያካትት፣

- ኢማን የሚለው ተነጥሎ ሲጠቀስ በውስጡ ኢስላም የሚለውን ያካትታል።

- የተጠቀሰው ኢህሳን የሚለው ብቻ ከሆነ ግን በውስጡ ኢስላምና ኢማን ይካተታሉ ።

## <u>የአምልኮ ምንነት፡-</u>

የአምልኮ ቋንቋዊ ትርጉም ራስን ዝቅ ማድረግ ማለት ሲሆን ኃይማኖታዊ ትርጉሙ ደግሞ ማንኛውም አላህ የሚወደው ነገር ቃልም ሆነ ተግባር ግልፅም ሆነ ስውር አምልኮ ይባላል።

- አምልኮ ሦስት ማዕዘናት አሉት እነሱም፡-

1- መውደድ፤

2- መፍራትና

3- መከጀል ናቸው።

ይህ ማለት አላህን በመውደድ፤ እዝነቱን በመከጀል እና ቅጣቱን በመፍራት መገዛት ማለት ነው ።

## የአምልኮ መስፈርቶች

ማንኛውም አምልኮ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ሁለት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው እነሱም፡-

1- ኢኽላስ ወይም አምልኮን ለአላህ ብቻ ማድረግ አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَمَا أُمِرُوا إِلا لِيَعْبُدُوا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ حُنَفَاءَ } (البينة : **5**) **.**

“ ኃይማኖትን ፍፁም ለአላህ ብቻ አድርገው ሊገዙት እንጂ አልታዘዙም” (አል-በይና: 5)

2- ሙታበዓ(መከተል) ይህም የሚረጋገጠው ማንኛውም ዒባዳ በአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ አስተምህሮና አሰራር መሰረት ሲፈፀም ብቻ ነው የአላህ መልዕክተኛ /ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

« مَنْ عَمِلَ عَمَلا لَيْسَ عَلَيْهِ أَمْرُنَا فَهُوَ رَدٌّ» .

“ ትዕዛዛችን የሌለበትን ተግባር በአምልኮ ስም ያከናወነ ስራው ተመላሽ ነው”ብለዋል።

# <u>አምልኮ በሁለት ይከፈላል፡-</u>

1- ተፈጥሮአዊ አምልኮና

2- ኃይማኖታዊ አምልኮ ናቸው።

ተፈጥሮአዊ በሆነው በአላህ ትዕዛዝ ስር ማደር ተፈጥሮአዊ አምልኮ ይባላ ይህም የአምልኮ ክፍል ሁሉንም ፍጥርታት ያካትታል።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

**{ إِنْ كُلُّ مَنْ فِي السَّمَاوَاتِ وَالأَرْضِ إِلا آتِي الرَّحْمَنِ عَبْدًا }( مريم :93 ) .**

"በሰማያትና በምድር ላይ ያሉ ፍጥረታት በሙሉ ለረህማን ባሪያዎች ሆነው ይመጣሉ"(መርየም: 93)።

ለአላህ ህግና ስርዓት ታዛዥና ተገዥ መሆን ደግሞ ኃይማኖታዊ አምልኮ ይባላል። ይህም የአምልኮ ክፍል በአላህ አምነው እሱን ብቻ ለሚገዙና መልእክተኞችን ለሚከተሉ ሰዎች የተለየ ማዕረግ ነው ።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

**{ وَعِبَادُ الرَّحْمَنِ الَّذِينَ يَمْشُونَ عَلَى الأَرْضِ هَوْنًا } (الفرقان: 63).**

" የረህማን ባሮች እነዚያ በምድር ላይ ረጋ ብለው የሚሄዱ ናቸው " (አል-ፉርቃን: 63)

<u>አምልኮን ለአላህ ብቻ በማድረግ ረገድ ዋና መለኪያና መመዘኛ፡-</u>

ማንኛውንም አምልኮ ለአላህ ብቻ ማድረግ ተውሂድ ይባላል ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት ደግሞ ማጋራት ይባላል ። አላህ እንዲህ ይላል፡-

**{ وَاعْبُدُوا اللَّهَ وَلا تُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا }(النساء : 36) .**

" አላህን ተገዙ በእሱም ምንንም አታጋሩ " (አኒሳእ: 36)

አላህ በሌላ አንቀፅ ላይም እንዲህ ይላል፡-

{ وَقَضَى رَبُّكَ أَلا تَعْبُدُوا إِلا إِيَّاهُ) ( الإسراء: **23**)

" ጌታህ እሱን ብቻ እንጂ ከእሱ ሌላ ማንንም አትገዙ በማለት አዘዘ (ወሰነ)" (አል-ኢስራእ: 23)

*- ዱዓን( ፀሎትን) ፤ፍርሐትን ፤እርድን ፤ስለትንና የመሳሰሉትን የአምልኮ ዘርፎች ከአላህ ሌላ ለሆነ አካል አሳልፎ መስጠት ከመንገድ (ከኢስላም) የሚያስወጣ የሽርክ ወንጀል ነው።

## የውዴታ ዓይነቶች፡-

ውዴታ አራት ዓይነቶች አሉት እነሱም፡-

1- አላህንና አላህ የሚወደውን ነገር ሁሉ መውደድ ከአምልኮ ይመደባል አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَالَّذِينَ آمَنُوا أَشَدُّ حُبًّا لِلَّهِ }(البقرة **165**) **.**

" እነዚያ ያመኑትም አላህን ከማንኛውም በላይ ይወዳሉ"(አልበቀራህ: 165)

2- ለአላህ እንጂ ለማንም የማይገባን ውዴታና ክብር ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት በአላህ እንደማጋራት ይቆጠራል አላህ እንዲህ ይላል፡-

{وَمِنَ النَّاسِ مَنْ يَتَّخِذُ مِنْ دُونِ اللَّهِ أَنْدَادًا يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ اللَّهِ } ( البقرة **165**)

"ከሰዎችም እንደ አላህ አድርገው የሚወዷቸውን ጣዖታት የሚገዙ አሉ" (አልበቀራህ: 165)።

3- ኃጢአትን ፤ በኃይማኖት ፈጠራን እና አላህ እርም ያደረጋቸውን ነገሮች መውደድ ከወንጀል ይመደባል፡-

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ إِنَّ الَّذِينَ يُحِبُّونَ أَنْ تَشِيعَ الْفَاحِشَةُ فِي الَّذِينَ آمَنُوا لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ فِي الدُّنْيَا وَالآخِرَةِ وَاللَّهُ يَعْلَمُ وَأَنْتُمْ لا تَعْلَمُونَ } (النور **19**)

"እነዚያ በአማኞች ላይ ፀያፍ ተግባር እንዲሰራጭና ስማቸውን ማጉደፍ የሚወዱ ሰዎች ለነሱ በዚች በቅርቢቱ ሕይወትና በመጨረሻይቱም ዓለም አሳማሚ የሆነ ቅጣት አለባቸው አላህም ያውቃል እናንተ አታውቁም " (አኑር: 19) ፡፡

4- ሚስቶችን፤ ልጆችን፤ ገንዘብንና የመሳሰሉትን መውደድ ተፈጥሮአዊ ውዴታ ይባላል ይህም ዓይነቱ ውዴታ የተፈቀደ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ زُيِّنَ لِلنَّاسِ حُبُّ الشَّهَوَاتِ مِنَ النِّسَاءِ وَالْبَنِينَ وَالْقَنَاطِيرِ الْمُقَنْطَرَةِ مِنَ الذَّهَبِ وَالْفِضَّةِ وَالْخَيْلِ الْمُسَوَّمَةِ وَالأَنْعَامِ وَالْحَرْثِ ذَلِكَ مَتَاعُ الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَاللَّهُ عِنْدَهُ حُسْنُ الْمَآبِ } (آل عمران : **14**).

"ሴቶችን፤ ወንድ ልጆችን፤ ከወርቅና ከብር የሆኑ ብዙ ገንዘቦችን፤ ለተመልካች የሚያስደስቱ ፈረሶችን፤ የቤት እንስሳትንና አዝእርትን መውደድ ለሰዎች ተዋበላቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች የቅርቢቱ ህይወት መገልገያና መጠቀሚያ ናቸው አላህ ከእርሱ ዘንድ ጥሩ መመለሻ አ"(አሊዒምራን: 14)፡፡

## ፍርሐት፡-

ችግር ሊያመጣ በሚችል ነገር መረበሽና መጨነቅ ፍርሐት ይባላል፡፡ እሱም ብዙ ዓይነቶች አሉት ከነሱም ዋና ዋናዎቹ፡-

1- ከአምልኮ ዘርፎች የሚቆጠር የፍርሐት ዓይነት ሲሆን እሱም አላህን ብቻ መፍራት ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَلِمَنْ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِ جَنَّتَانِ }( الرحمن : **46**) .

" ከጌታውም ፊት(እንደሚቆም አምኖና ፈርቶ መልካምን የሰራ ሰው) ሁለት ገነቶች አሉት"(አረሕማን: 46)

<u>አላህን መፍራት በሁለት ይከፈላል</u>፡-

አንደኛ- ከወንጀል ለመራቅ የሚያግዝና ግዴታዎችን ለመፈፀም የሚያነሳሳ ከሆነ ፍርሐቱ የተወደደና የተመሰገነ ሲሆን፡-

ሁለተኛ- ከአላህ እዝነትና ምሕረት ተስፋ የሚያስቆርጥ ከሆነ ደግሞ ፍርሐቱ የተወገዘና የተጠላ ይሆናል።

2- ተናካሽ የሆኑ የዱር እንስሳትን ፤ጠላትን ፤ግፈኛ ባለስልጣንና የመሳሰሉትን መፍራት ደግሞ ከአምልኮ ጋር ግንኙነት የሌለው ተፈጥሮአዊ ፍርሐት በመባል ይታወቃል እሱም የተፈቀደ ነው።

3- አላህ እንጂ ሌላ አካል ሊያደርሰው የማይችለውን ችግር ለምሳሌ፡- ድህነትን፤ ህመምን፤ አለመውለድንና የመሳሰሉትን ችግሮች ከአላህ ሌላ የሆነ አካል ያደርስብኛል ብሎ መፍራት ከትልቁ ሽርክ ይመደባል ይህም ስውሩ ፍርሃት በመባል ይታወቃል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ فَلا تَخَافُوهُمْ وَخَافُونِ إِنْ كُنْتُمْ مُؤْمِنِينَ } ( آل عمران : **175**) .

" አትፍሯቸው ትክክለኛ አማኞች ከሆናችሁ እኔን ብቻ ፍሩ"(ኣሊ-ዒምራን: 175)።

4-ሰዎችን በመፍራት አላህ ግዴታ ያደረገውን አለመፈፀም ወይም የከለከለውን መስራት የተወገዘ ፍርሐት ይሆናል።

{ فَلا تَخْشَوُا النَّاسَ وَاخْشَوْن } ( المائدة : **44**)

" ሰዎችንም አትፍሩ እኔን ብቻ ፍሩ" (አል-ማኢዳ: 44)

# ተስፋ፡-

መልካምን ነገር መመኘትና መከጀል ተስፋ ይባላል። እሱም ሦስት ክፍሎች አሉት፡-

1- አላህን ብቻ መከጀልና ተስፋ ማድረግ ከአምልኮ የሚመደብ ተስፋ ሲሆን እሱም ሁለት ክፍሎች አሉት፡-

ሀ - ተስፋው ከመልካም ስራ ጋር የተጣመረና የተዛመደ ከሆነ የተመሰገነና የተወደደ ተስፋ ይባላል ። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ فَمَنْ كَانَ يَرْجُو لِقَاءَ رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْ عَمَلا صَالِحًا وَلا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِ أَحَدًا }

(الكهف :**110**).

" የጌታውንም መገናኘት የሚከጅል ሰው፤ መልካምን ይሥራ፡፡ በጌታውም መገዛት ማንንም አያጋራ"(አል-ከህፍ: 110)

ለ - ተስፋው ከመልካም ስራ ጋር የተዛመደ ካልሆነ ደግሞ የተጠላና የተወገዘ ከንቱ ምኞት ይባላል።

2- ሰዎች ማድረግ በሚችሉት ነገር አንዱ ከሌላው መከጀል የተፈቀደ ነው ይህም ተፈጥሮአዊ ተስፋ ይባላል።

3- ከአላህ ውጭ ማንም አካል መስጠት የማይችለውን ነገር ለምሳሌ፡- ጤናን፤ ሀብትን፤ ልጅንና የመሳሰሉትን ነገሮች ከአላህ ሌላ ከሆነ አካል መከጀል በአላህ የማጋራት ወንጀል ይሆናል።

# ተወኩል ወይም መመካት፡-

የተወኩል ቋንቋዊ ትርጉም መጠጋት (መደገፍ) ማለት ሲሆን ኃይማኖታዊ ትርጉሙ ደግሞ ልቦናን በአላህ ላይ ብቻ እንዲመካና እንዲፀና ማድረግ ተወኩል ይባላል ። ተወኩል(መመካት) በሦስት ይከፈላል እነሱም፡-

አንደኛ - ከአምልኮት የሚመደብ ተወኩል ሲሆን እሱም በአላህ ላይ ብቻ መመካት ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَعَلَى اللَّهِ فَتَوَكَّلُوا إِنْ كُنْتُمْ مُؤْمِنِينَ } ( المائدة :23) .

" አማኞችም ከሆናችሁ በአላህ ላይ ብቻ ተመኩ " (አል-ማኢዳ: 23)

ይህ የተወኩል ክፍል አምልኮ ይሆን ዘንድ ሦስት ነገሮች መሟላት አለበት እነሱም፡-

1- በአላህ ላይ በእርግጠኝነት መመካት፤

2- በአላህ ላይ ሙሉ እምነት መኖር እና ማንኛውም ነገር በአላህ እጅ መሆኑን ማመን፤

3- የተፈቀዱ ቁሶችንና ምክንያቶችን መስራት ናቸው ።

ሁለተኛ - ከአላህ ውጭ በሆነ አካል ላይ መመካትና በቁሶች ወይም በምክንያቶች ላይ መመካት ከሽርክ ይቆጠራል።

ሦስተኛ- መተካት ወይም መወከል ሲሆን ይህም አንድ ሰው ሌላውን ግለሰብ የግል ስራውን ያከናውንለት ዘንድ መተካት/መወከል/ ነው። ይህም የተፈቀደ ነው ።

**<u>በመመካትና በመወከል መካከል ያለው ልዩነት፡-</u>**

1- ተወኩል ወይም መመካት ውስጣዊና የልቦና ተግባር ሲሆን እሱም ከአምልኮት ጋር ተያያዥነት አለው ።

2- መተካት ወይም መወከል ግን ከአምልኮ ጋር ግንኙነት የሌለው ውጫዊ ስራ ነው ።

## ዱዓ ወይም ልመና፡-

ዱዓ ከአምልኮት ዘርፎች ትልቁን ሥፍራ ይይዛል  እሱም በሁለት መልኩ ይገለፃል፡-

አንደኛው- በጥያቄ መልኩ የሚገለፅ ልመና ነው ለምሳሌ፡-

አላህ ሆይ! እዘንልኝ ፤ ማረኝ እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በማንሳት አላህን መለመንና መማፀን፤

ሁለተኛው- በሥራ የሚገለፅ የጸሎት ዓይነት ነው ለምሳሌ፡- ሦላትን በመስገድ ፤ ዘካን በመስጠት ፤ ፆምን በመፆም ፤ ሐጅን በማድረግ ፤ ሶደቃን በመስጠትና የመሳሰሉትን መልካም ስራዎች በማከናወን የሚገለፅ የአምልኮ  ተግባር ነው። እነዚህም የአምልኮት ዘርፎች ዱዓ በሚል ስያሜ የተሰየሙበት ምክንያት አንድ ሰው እነዚህንና የመሳሰሉትን መልካም ስራዎች ሲፈጽም የአላህን ውዴታና ጀነትን ፈልጎ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ የአላህን ቁጣና ጀሃነምን ፈርቶ ነው።

ልመና በሁለቱም ክፍሎቹ ለአላህ ብቻ መሆን ያለበት ትልቅ የአምልኮት ዘርፍ ነው። ስለዚህ ይህን ትልቅ አምልኮ ከአላህ ሌላ ለሆነ አካል አሳልፎ የሰጠ ሰው አጋሪ( ከሃዲ) ይባላል።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَمَنْ يَدْعُ مَعَ اللَّهِ إِلَهًا آخَرَ لا بُرْهَانَ لَهُ بِهِ فَإِنَّمَا حِسَابُهُ عِنْدَ رَبِّهِ إِنَّهُ لا يُفْلِحُ الْكَافِرُونَ } ( المؤمنون : 117 ) .

“ ለአምላክነቱ ማስረጃ ሊኖረው የማይችልን አካል ከአላህ ጋር የሚገዛ ሰውም ምርመራው ከጌታው ዘንድ ብቻ ነው፡፡ እነሆ ከሓዲዎች አይድኑም ”(አል-ሙእሚኑን: 117)።

በሌላም አንቀፅ ላይ  አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَأَنَّ الْمَسَاجِدَ لِلَّهِ فَلا تَدْعُوا مَعَ اللَّهِ أَحَدًا } (الجن : 18) .

“ መስገጃ ቦታዎችም የአላህ ብቻ ናቸው (በውስጣቸውም) ከአላህ ጋር ማንንም አትገዙ( አትፀልዩ)”(አል-ጅን: 18)

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ፡-

« الدُّعَاءُ هُوَ العِبَادَةُ »

“ ዱዓ ኢባዳ (አምልኮ) ነው ” ብለዋል ፡፡

## ሩቅያ/የበሽታመከላከያ/፡-

ሩቅያ በቋንቋ ደረጃ መጠበቂያ ወይም መከላከያ ማለት ሲሆን ሃይማኖታዊ ትርጉሙ ደግሞ በበሽተኛው ላይ የሚነበቡ የቁርኣን አንቀፆች ፣ዚክሮችና ዱዓዎች ማለት ነው፡፡

ሩቅያ ሁለት ዓይነቶች አሉት እነሱም፡-

አንደኛው- የሚከተሉትን ሦስት መስፈርቶች ካሟላ የተፈቀደ ሲሆን እነሱም

1- በአረበኛ ቋንቋና ትርጉሙ በሚታወቅ ነገር መሆን፣

2- በአላህ ቃል(በቁርኣን)፤ በስሞቹና በባህርያቱ መሆን፣

3- ሙሉ በሙሉ በበሽታ መከላከያ ላይ አለመመካት እና መከላከያው በአላህ ፍቃድ እንጂ በራሱ ጊዜ ለውጥ ወይም ፈውስ እንደማያመጣ ማመን ናቸው፡፡

የአላህ መልእክተኛ /ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም/ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፣-

«اعْرِضُوا عَلَيَّ رُقَاكُمْ، لا بَأْسَ بِالرُّقَى مَا لَمْ يَكُنْ فِيهِ شِرْكٌ " .

“ የበሽታ መከላከያችሁን አሳዩኝ (አቅርቡልኝ) የበሽታ መከላከያ በውስጡ የማጋራት ተግባር እስከሌለበት ድረስ የተፈቀደ ነው ” ብለዋል ።

ሁለተኛው- ከእነዚህ መስፈርቶች አንዱ ከተጓደለ መከላከያው የማጋራት ወንጀል ይሆናል።

የአላህ መልእክተኛ /ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም/ አቡዳውድ እና አህመድ በዘገቡት ሐዲስ፡-

« إِنَّ الرُّقَى، وَالتَّمَائِمَ، وَالتِّوَلَةَ شِرْكٌ ».

“ያልተፈቀዱ የበሽታ መከላከያዎች፤ ህርዞች እና መስተፋቅር በአላህ የማጋራት ኃጢአት ናቸው ” ብለዋል ።

## <u>ተማኢም(ህርዞች)፡-</u>

በሕፃናትና  በእንስሳት አንገት ላይ ከዐይን ለመከላከል በሚል የሚታሰር ነገር ህርዝ ይባላል።

ህርዝ በሁለት ተከፍሎ ይታያል። እነሱም፡-

አንደኛ- ከቁርኣንና ነቢያዊ ዱዓ( ፀሎቶች) የሚዘጋጅ ሲሆን ይህ የህርዝ ዓይነት ይፈቀዳል  ወይስ አይፈቀድም በሚል  ዑለሞች ሁለት አስተያየቶች አሏቸው። ይሁን እንጂ ትክክለኛውና አመዛኙ አይቻልም የሚለው ነው። ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች ይጠቅሳሉ፡-

1- ህርዝን የሚከለክሉት ሐዲሶች አጠቃላይነት ስላላቸው፤

2- የሽርክ በሮችን ለመዝጋት ስለሚረዳ። ምክንያቱም ሰዎች በዚህ አስታከው ሽርክ አዘል ነገሮችን ሊያስሩ(ሊጠቀሙ)ስለሚችሉ፤

3- የቁርኣንና ነቢያዊ ዱዓዎችን ክብር ለመጠበቅ ሲባል" ምክንያቱም አንድ ሰው እነሱን አስሮ (አንጠልጥሎ) ወደ ተለያዩ ቆሻሻ ሥፍራዎች ሊገባ ስለሚችል ።

ሁለተኛ- ከቁርአንና ከነቢያዊ ዱዓ ውጭ በሆነ ነገር የሚሰራ ለምሳሌ፡- በሰይጣናት ስም፤ ትርጉማቸው በማይታወቅ ፁሁፎች እና በሰንጠረዦች አማካኝነት የሚሰራ ህርዝ ነው ። ይህ የህርዝ ዓይነት ከአላህ ሌላ በሆነ ነገር ማመንን ስለሚያስከትል የተከለከለና ከከፍተኛው የማጋራት ኃጢኣት ይመደባል።

ከዚህ የምንማረው ዋና ቁም ነገር ህርዝ ከቁርኣን ከሆነ የተጠላ መሆኑንና ከቁርኣን ሌላ ከሆነ ደግሞ የማጋራት ወንጀል መሆኑን ነው። የአላህ መልእክተኛ /ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም/ አቡዳውድና አህመድ በዘገቡት ሐዲስ፡-

«إِنَّ الرُّقَى، وَالتَّمَائِمَ، وَالتِّوَلَةَ شِرْكٌ»

“ ያልተፈቀዱ የበሽታ መከላከያዎች፤ህርዞች እና መስተፋቅር በአላህ የማጋራት ኃጢኣት ናቸው ” ብለዋል ።

## በረከትን ወይም ረድኤትን መፈለግ፡-

በረከትን መፈለግ በሁለት ይከፈላል እነሱም፡-

፩ኛ- የተፈቀደ ሲሆን ይኸውም፡-

- በአላህ መልእክተኛ/ﷺ/ አካል፤ በፀጉራቸው እና በላበታቸው በረከትን/ረድኤትን/ ማገኘት ሲሆን ይህም በህይወት በነበሩበት ዘመን የተለየና የተገደበ ነው።

- ቅዱሳን በሆኑ ሥፍራዎች ለምሳሌ ፡- መካ በሚገኘው በተከበረው መስጂድ ፤ መዲና በሚገኘው በነቢዩ /ﷺ/ መስጂድ እና በሌሎችም ቅዱሳን ሥፍራዎች የተፈቀዱ ኢባዳዎችን በማድረግ ከአላህ በረከትን ማገኘት።

- አላህ በደረጃ ባበለጣቸው ወራትና ቀናት ለምሳሌ፡- በረመዷን ወር፤ ከዙል ሂጃ ወር በአስሮቹ ቀናትና ሌሊቶች፤ በተከበረችው ሌሊት(ለይለቱ- አል-ቀድር)ና በመሳሰሉት ወራትና ቀናት የተፈቀዱ ዒባዳዎችን በማድረግ ከአላህ ረድኤትንና በረከትን ማገኘት፤

- አላህ በረከት ያደረጋቸውን ምግቦች ለምሳሌ፡- ዘይት ዘይቱንን(የወይራ ዘይት) ፤ ማርን ፤ጥቁር አዝሙድን ፤ የዘምዘም ውሃን እና የመሳሰሉትን በመጠቀም በረከትን(ረድኤትን) ማገኘት ነው።

2ኛ- የተከለከለ ሲሆን እሱም፡-

- የተቀደሱ ሥፍራዎችን በመሳም ፤ በመንካት፤ ከእነሱ ጋር ግንኙነት ያለውን ነገር ቆርጦ መያዝ እና አፈሩን በመጠጣት ወይም በመሞቅ በረከትን ወይም ፈውስን ለማገኘት ማሰብ፤

- በደጋግ ሰዎች ቅሪት፤ በመቃብራቸው እና ታሪካዊ በሆኑ ሥፍራዎች ለምሳሌ ፡- ነቢዩ /ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም/ በተወለዱበት ሥፍራ ፤ ሂራ በተባለው ተራራ እና በመሳሰሉት ሥፍራዎች በረከትን ለማገኘት መሞከር።

- የአላህ መልእክተኛ /ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም/ የተወለዱበትን ቀን ወይም ሌሊት፤ ወደ በይተል- መቅዲስ እና ከዚያም ወደ ሰማይ የወጡበትን ሚዕራጅ በመባል የሚታወቀውን ሌሊት፤ ከሻዕባን ወር አስራ አምስተኛዋን ሌሊት እና የመሳሰሉትን ቀናትና ሌሊቶች በማክበር በረከትን(ረድኤትን) ለማገኘት ማሰብ ናቸው።

**<u>በረከትን(ረድኤትን) ሊገድቡ የሚችሉ ወሳኝ ነጥቦች፡-</u>**

1- በረከትን ወይም ረድኤትን መፈለግ የአምልኮ ዘርፍ መሆኑንና አምልኮ ደግሞ በማስረጃ መወሰን እንጂ መፍጠር የማይቻል መሆኑን በሚገባ መረዳት፤

2- በረከት(ረድኤት) በሙሉ የአላህ መሆኑንና መስጠትም ሆነ መንሳት የሚችለው እሱ ብቻ መሆኑን አምኖ ከእርሱ ብቻ መጠየቅ እንጂ ከሌላ አካል መጠየቅ እንደማይፈቀድ ማወቅ፤

3- በረከት የሚያስገኝን ነገር ሲያከናወን ህጋዊ በሆነ አሰራር መፈፀም ናቸው።

**<u>ምክንያቶችን በመጠቀም ረገድ መኖር ያለባቸው ወሳኝ ነጥቦች፡-</u>**

1ኛ- ምክንያቶችን ያስገኘና ምክንያት እንዲሆኑ ያደረገው አላህ ብቻ ስለሆነ በአላህ ላይ እንጂ በምክንያቶች ላይ አለመመካት፤

2ኛ- ምክንያቶች ከአላህ ውሳኔ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ማወቅና መረዳት ናቸው።

**አንድ ነገር ምክንያት መሆኑ በሁለት መንገድ ይታወቃል፡-**

1- በቁርዓንና በሓዲስ አማካኝነት ለምሳሌ ፡- የማር መድሃኒትነት በቁርአን የተነገረ ሲሆን የጥቁር አዝሙድ መድሃኒትነት በሐዲስ ተዘግቧል።

2- በትክክለኛ ሙከራም ሊታወቅ ይችላል።

## ተወሱል ወይም መጠጋት፡-

ተወሱል(መጠጋት) በሁለት ይከፈላል እነሱም፡-

አንደኛ- የተፈቀደ ሲሆን እሱም በሦስት መልኩ ይገለፃል።

1- አላህን በስሞቹና በባህሪያቱ በማወደስና በመለመን ወደ እርሱ መጠጋት፤

2- አንድ ሰው የሰራውን መልካም ስራ በማንሳት አላህን መማፀንና ወደ እሱ መጠጋት፤

3- በሕይወት ባሉ ደጋግ ሰዎች ዱዓ(ፀሎት) ወደ አላህ መቃረብ ናቸው ።

ሁለተኛ- የተከለከለ የተወሱል ዓይነት ሲሆን እሱም ከተፈቀዱት የተወሱል ዓይነቶች ውጭ በሆነ ነገር ወደ አላህ ለመጠጋት መሞከር ነው። ይህም በሦስት ተከፍሎ ይታያል፡-

1- በሰዎች ትልቅነትና ክብር ወደ አላህ ለመጠጋት መሞከር፣

2- ወደ አላህ ለመጠጋት ለአላህ ወዳጆችና ለደጋግ ሰዎች መሳል ፤

3- በአላህ ወዳጆች መቃብር አካባቢ በመቀመጥ እና በማረድ ወደ አላህ ለመቃረብ ማሰብ ናቸው ።

## **እርድ፡-**

እርድ ሦስት ክፍሎች አሉት እነሱም፡-

1- የተፈቀዱ አምልኳዊ እርዶች፤

2- ለምግብነት ብቻ የሚታረዱ እርዶች፣

3- የማይፈቀዱ አምልኳዊ እርዶች ናቸው።

## **አንደኛ -የሚፈቀዱ አምልኳዊ እርዶች፡-**

1- ለዒደል- አድሃ ማረድ፤

2- ለአላህ የተሳለውን የእርድ ስለት ማረድ፤

3 - በሐጅ ወቅት ሶደቃ ለመስጠት ማረድ፣

4 - በሐጅና ዑምራ ስራ ላይ እያለ ላጠፋው ጥፋት ማካካሻ ማረድ፣

5 -ልጅ ሲወለድ ለዓቂቃ ማረድ፤

6 - እንግዳን ለማስተናገድ ማረድ እና የመሳሰሉት ናቸው ።

ሁለተኛ - ለመመገብ እና ለመሸጥ ማረድ ሲሆን ይህ ዓይነት እርድም የተፈቀደ ነው ።

ሦስተኛ- የማይፈቀዱ አምልኳዊ እርዶች፡-

1 - ከአላህ ውጭ ለሚመለኩ ለባዕድ አማልክት ማረድ፣

2- ለአጋንንት ፤ ለመቃብር፤ ለአድባር(ለቆሌ)እና ለመሳሰሉት ነገሮች ማረድ፤

3 - በአዲስ ቤት ለመኖር ሲፈልግ ከመገባቱ በፊት ከአጋንንት ለመከላከል በሚል ስሜት ማረድ፣

4- ሁለት ተጋቢዎች(ሙሽሮች) ወደ ቤት ሲገቡ ደሙን ረግጠው ይገቡ ዘንድ ማረድ፣

5- ከአላህ ሌላ በሆነ አካል ስም ማረድ እና የመሳሰሉት ናቸው።

➯ ከዚህ የምንረዳው ዋና ቁም ነገር

1- አምልኳዊ የሆነውን እርድ ከአላህ ሌላ ለሆነ አካል አሳልፎ መስጠት የማይፈቀድ መሆኑንና ፣

2- ከአላህ ውጭ ለሆነ አካል ማረድ ከአላህ እዝነት የሚያርቅና የሚያስረግም ከፍተኛ የማጋራት ወንጀ መሆኑን ነው።

አላህ እንዲህ ይላል፤

{ قُلْ إِنَّ صَلاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ } ( الأنعام : **162**).

"ስግደቴ ፤ እርዴ(መገዛቴ) ፤ ህይወቴና ሞቴም ለዓለማት ፈጣሪ ለአላህ ብቻ ነው በል" (አል-አንዓም: 162) ።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

{ لعن اللّٰهُ مَنْ ذَبَحَ لِغَيْرِ اللّٰهِ،}.

" ከአላህ ሌላ ለሆነ አካል የሚያርድ ሰው አላህ ይረግመዋል" ብለዋል።

## <u>ነዝር (ስለት)፡-</u>

ስለት አላህ ብቻ መሆን ያለበትና ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት የማይፈቀድ የአምልኮ ዘርፍ ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ يُوفُونَ بِالنَّذْرِ} ( الإنسان : 7).

" እነዚያ የአላህ ባሮች ለእርሱ የተሳሉትን ስለት ይሞላሉ"(አል-ኢንሳን: 7)

ከአላህ ውጭ የሆነን አካል ለማክበርና ወደ እርሱ ለመቃረብ ብሎ መሳል በአላህ የማጋራት ወንጀል ይሆናል። ለምሳሌ ፡-ልጅ ከተወለደልኝ፤ በሽተኛው ከዳነልኝ ወዘተ... እገሌ ከተባለው ወሊይ ቀብር ዘንድ እንደዚህ ዓይነት በግ ወይም ከብት አርዳለሁ ብሎ መሳል የሽርክ ተግባር ነው።

## እርዳታንና ጥበቃን መለመን፡-

እነዚህ ነገሮች ከአላህ ብቻ መጠየቅ ያለባቸው የአምልኮ ዘርፎች ናቸው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ }( الفاتحة:5) .

" አንተን ብቻ እንገዛለን አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን " (አልፋቲሃ: 5) አላህ በሌላም አንቀፅ ላይ እንዲህ ይላል፡-

{ إذ تَسْتَغِيثُونَ رَبَّكُمْ فَاسْتَجَابَ لَكُمْ } (الأنفال:9) .

"ፈጣሪያችሁን እርዳታ በጠየቃችሁ ጊዜና እሱም ወዲያውኑ ምላሽ በሰጣችሁ ጊዜ ያለውን አስታውሱ " (አል-አንፋል: 9)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ النَّاسِ } (الناس: 1) .

" በሰዎች ፈጣሪ ( በአላህ) እጠበቃለሁ በል " (አናስ: 1) ።

**ከአላህ ሌላ ከሆነ አካል እርዳታንና ጥበቃን መለመን በሁለት መልኩ ይታያል፡-**

አንደኛው፡-አራት መስፈርቶችን ካሟላ የተፈቀደ ሲሆን እነሱም፡-

1- እገዛ (እርዳታ) የሚጠየቅበት ነገር ሰዎች ማድረግ የሚችሉት መሆን፡- ስለዚህ ጤናን፤ ልጅን፤ሀብትን፤ እምነትንና የመሳሰሉትን ከአላህ ሌላ ከሆነ አካል መጠየቅ አይፈቀድም ምክንያቱም እነዚህንና የመሳሰሉትን መስጠት የሚችለው አላህ ብቻ ስለሆነ፤

2- እርዳታ የሚጠየቅበት ነገር በሰዎች ሃይል ሊፈፀም የሚችል መሆን፤

3 - እርዳታ/እገዛ/ የሚጠየቀው አካል በሕይወት መኖር እና

4- እርዳታ የሚጠየቀው አካል ጥያቄውን መስማት የሚችል መሆን ናቸው ።

ሁለተኛው- የማይፈቀድ ሲሆን እሱም በመጀመሪያው ነጥብ ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ሳያሟላ ሲቀር ነው ።

## ምልጃ፡-

ምልጃ በሁለት ይከፈላል፡-

አንደኛው- ኢስላም እውቅና የሰጠውና ያፀደቀው ምልጃ ሲሆን ይኸውም ሁለት መስፈርቶችን ሲሟላ ነው።

1- አማላጁ እንዲያማልድ አላህ የፈቀደለት መሆን፣

2- የአማላጁና ምልጃ የሚጠየቅለት ግለሰብ ስራ አላህ የሚወደው መሆን ናቸው።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ مَنْ ذَا الَّذِي يَشْفَعُ عِنْدَهُ إِلا بِإِذْنِهِ } (البقرة:255 ).

“ በአላህ ፍቃድ  እንጂ  ማንም ከእርሱ ዘንድ  የሚያማለድ የለም ” አል-በቀረህ: 255)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَكَمْ مِنْ مَلَكٍ فِي السَّمَاوَاتِ لا تُغْنِي شَفَاعَتُهُمْ شَيْئًا إِلا مِنْ بَعْدِ أَنْ يَأْذَنَ اللَّهُ لِمَنْ يَشَاءُ وَيَرْضَى} ( النجم :**26**)

“በሰማያት ውስጥ በርካታ መላእክት አሉ እነዚህ መላእክት አላህ ለፈለገውና ለወደደው ሰው ከፈቀደ በኋላ እንጂ ማንንም ማማለድ አይችሉም ” (አነጅም: 26)፡፡

ሁለተኛው- ምልጃው በመጀመሪያው ነጥብ ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ያላሟላ ከሆነ የተከለከለ ይሆናል ፡፡

**➪ <u>ከሰዎች ምልጃን መጠየቅ ይፈቀድ ዘንድ ሁለት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-</u>**

1ኛ- ምልጃ የሚጠየቀው ግለሰብ በህይወት ያለና የተጠየቀውን ነገር ማድረግ የሚችል መሆንና፤

2ኛ- ምልጃ የተጠየቀበት ጉዳይ በሰዎች አቅምና ችሎታ የሚፈፀም መሆን ናቸው፡፡

## <u>መቃብርን መዘየር/መጎብኘት/፡-</u>

ቀብርን መዘየር በሦስት ይከፈላል፡-

አንደኛ- ጉብኝቱ ለሚከተሉት ዓላማዎች ከሆነ፡-

1- የመጨረሻውን ጉዞ ለማስታወስ፤

2- በመቃብር ውስጥ ለሚገኙ ለሙስሊም ሙታን ሰላምታን ለማቅረብና

3- ለሙታን ዱዓ ለማድረግ ከሆነ የተፈቀደ ይሆናል።

ሁለተኛ- ጉብኝቱ ወይም ዚያራው ለሚከተሉት ዓላማዎች ከሆነ ደግሞ ለምሳሌ፡-

1- ከቀብሩ ዘንድ ሆኖ አላህን ለመገዛት፣

2- በቀብሩ ውስጥ ከሚገኘው ሟች በረከትን/ረድኤትን/ ለመጠየቅ፣

3- ቁርኣን ቀርቶ ምንዳውን ለቀብሩ ባለቤት ለመስጠት እና ለመሳሰሉት መጥፎ ዓላማዎች ከሆነ ተውሂድን የሚያጓድል ብሎም ወደ ማጋራት ወንጀል የሚያመራ የፈጠራ ተግባር ይሆናል።

3ኛ - ዚያራው/ጉብኝቱ/ ከአምልኮት ዘርፎች ለምሳሌ ፡- እንደ- ዱዓ፤ እርዳታ መጠየቅ፤ ስለት፤ ማረድና የመሳሰሉትን አምልኮዎች ለቀብሩ ባለቤት አሳልፎ ለመስጠት ከሆነ ዚያራው ተውሂድን በቀጥታ የሚያፈርስ የማጋራት ተግባር ይሆናል።

## <u>ድግምት፡-</u>

ድግምት በአላህ ውሳኔ በአካልም ሆነ በስነልቦና ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ትልቅ ኃጢአት ነው።

ድግምት ሁለት ዓይነት ነው ፡-

1- ከእስልምና ሃይማኖት የሚያስወጣና ሟርተኛው በግድያ እንዲቀጣ የሚያደርግ ከፍተኛ የማጋራት ወንጀል ሲሆን እሱም በሰይጣናት በመታገዝ የሚሰራ የድግምት ዓይነት ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَمَا يُعَلِّمَانِ مِنْ أَحَدٍ حَتَّى يَقُولا إِنَّمَا نَحْنُ فِتْنَةٌ فَلا تَكْفُرْ }( البقرة :102).

"ድግምትን ያስተምሩ የነበሩ ሁለት አስተማሪዎችም " እኛ ፈተናዎች ነን ድግምትን በመማር አትካድ በማለት ሳያስጠነቅቁ በፊት ማንንም አያስተምሩም " (አልበቀረህ: 102)።

ይህ አንቀፅ የሚያስረዳው ድግምትን መማር ከኢስላም የሚያስወጣ ክህደት መሆኑን ነው ።

2- ከእስልምና ሃይማኖት ባያስወጣም ነገር ግን ደጋሚው ወይም ሟርተኛው በሰዎች ላይ የሚያደርሰውን ችግር ለመቅረፍ ሲባል እንዲገደል የሚያደርግ ትልቅ ወንጀልና አመፅ ሲሆን እሱም ከተለያዩ መድሃኒቶች የሚሰራ የሟርት ዓይነት ነው ።

## <u>ድግምትን መፍታት (ማክሸፍ)፡-</u>

ድግምትን መፍታት (ማክሸፍ) በሁለት ተከፍሎ ይታያል፡-

1ኛ- ድግምትን በድግምት መፍታት (ማክሸፍ) የተከለከለና የሰይጣን ስራ ሲሆን፤

2ኛ- ኃይማኖታዊ መከላከያዎችንና የተፈቀዱ መድሃኒቶችን በመጠቀም ድግምትን መፍታት (ማክሸፍ) ግን የተፈቀደ ነው ።

## ➩<u>ከሟርተኞች ማስጠንቀቅና የነሱን ጉዳይ ለሚመለከተው አካል መናገር፡-</u>

*- የድግምተኞችን ጉዳይ ለሚመለከተው አካል መጠቆምና ሙስሊሞች ከእነሱ እንዲጠንቀቁ ማድረግ ኢስላማዊ ግዴታ ነው።

## <u>የድግምተኛ ምልክቶች፡-</u>

1ኛ- የበሽተኛውንና የእናቱን ስም መጠየቅ፣

2ኛ- ከበሽተኛው አካል ጋር ግንኙነት ያላቸውን ነገሮች ለምሳሌ፡- ከቀሚስ፤ ከቢጃማ፤ ከራስ ማሰሪያ፤ ከውስጥ ልብስና ከመሳሰሉት ቆርጦ ማስቀረት፤

3- ሰንጠረዦችን ማስመር፤

4- ትርጉሙ ማይታወቅ ነገር ማነብነብ፤

5- በሽተኛው ወረቀቶችን አቃጥሎ ጪሱን እንዲታጠን ማዘዝ፣

6- የተለየ የቆዳ ቀለም ያለው የቤት እንስሳ አስመጥቶ የአላህን ስም ሳያወሳ አርዶ ህመም ያለበትን የበሽተኛውን የሰውነት ክፍል  በደም መቀባት፣

7- በሽተኛው አራት መዓዘንና በውስጡ ፊደሎች ወይም ቁጥሮች ያሉበትን ሂጃብ ወይም ልብስ እንዲለብስ ማዘዝ፤

8- በሽተኛው የተለያዩ ነገሮችን በጉድጓድ ውስጥ እንዲጨምር/ እንዲቀብር ማዘዝ እና የመሳሰሉት ናቸው ።

**ማሳሰቢያ፡-**

ለሰዎች የህክምና አገልግሎት እሰጣለሁ የሚል አካል ከእነዚህ ምልክቶች አንዱንም ቢሆን ከተጠቀመ  ድግምተኛ መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

## ጠንቋይና አዋቂ ነኝ ባይ፡-

በሰይጣናት በመታገዝ ወደፊት ሊከሰት የሚችልን ነገር ወይም የተሰረቀና የጠፉን ነገር ሥፍራ አውቃለሁ ብሎ የሚናገር ሰው ጠንቋይ ይባላል ብያኔውም ቁርኣንን የማስተባበል  ክህደት ነው። ምክንያቱም አላህ በቁርኣን እንዲህ ስለሚል፡-

**{ قُلْ لا يَعْلَمُ مَنْ فِي السَّمَاوَاتِ وَالأَرْضِ الْغَيْبَ إِلا اللَّهُ } (النمل : 65).**

" አላህ እንጂ በሰማያትና በምድር ያሉ ፍጥረታት በሙሉ ከሰዎች ድብቅና ስውር የሆነን ነገር አያውቁም በል " (አነምል: 65)

**አንድ ጠንቋይ ከሌላው የሚለይበት የአሰራር ስልትና ተጨማሪ ስያሜው፡-**

1ኛ- የሩቅ ሚስጥሮችን አውቃለሁ ብሎ ሲናገር በጅኖች በመታገዝ ከሆነ ጠንቋይ ይባላል።

2ኛ- በከዋክብት አማካኝነት ከሆነ ደግሞ ሙነጂም/ ኮከብ ቆጣሪ/ ይባላል።

3ኛ-የጠፉና የተሰረቀን ነገር ሥፍራ የሚናገር ከሆነ አውቃለሁ ባይ ይባላል።

4ኛ- በመሬት ላይ በማስመር ከሆነ ደግሞ ረማል (ጠጠር ቆጣሪ) ይባላል ።

## ወደ ጠንቋይ የመሄድ ብይን፡-

ወደ ጠንቋይ የመሄድ ብይን በሁለት መልኩ ይታያል።

1ኛ- ከጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ስለ አንድ ነገር የጠየቀ ሰው የጥያቄውን መልስ እውነት ብሎ ባይቀበልም በመሄዱ ብቻ የአርባ ቀን ሦላቱ/ስግደቱ/ ተቀባይነትን ያጣል። የአላህ መልእክተኛ /ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም/ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

"من أَتَى عَرَّافًا فَسَأَلَهُ عَنْ شَيْءٍ، لَمْ تُقْبَلْ لَهُ صَلاةٌ أَرْبَعِينَ لَيْلَةً"

“ ወደ ጠንቋይ ሄዶ ስለ አንድ ነገር የጠየቀ ሰው ያአርባ ቀን ስግደቱ ተቀባይነት አያገኝም ” ብለዋል።

2ኛ- ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ የጠየቀና የተሰጠውን መልስ እውነት ብሎ የተቀበለ ሰው በቁርኣን እንደ ካደ ይቆጠራል።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ሃኪምና ሌሎችም በዘገቡት ሐዲስ፡-

" من أتى كَاهِنًا، فَصَدَّقَهُ بِمَا يَقُولُ، فَقَدْ كَفَرَ بِمَا أُنْزِلَ عَلَى مُحَمَّدٍ ".

"ወደ ጠንቋይ ሄዶ ጠንቋዩ የሚናገረውን እውነት ብሎ የተቀበለ ሰው በሙሀመድ ላይ በተወረደው ቁርዓን በእርግጥ ካደ" ብለዋል ።

## በገድ ማመን፡-

በገድ ማመን ተውሂድን የሚያበላሽ የማጋራት ኃጢአት ነው።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ አቡ ዳውድና ትርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ፡-

«الطِّيَرَةُ شِرْكٌ».

" በገድ ማመን የማጋራት ወንጀል ነው " ብለዋል።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ በገድ ማመን በኢስላም የማይፈቀድ መሆኑን ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

« لاعدوى و لا طِيَرَةَ، وَلاَ هَامَةَ وَلاَ صَفَرَ».

"አንድ በሽታ በራሱ ጊዜ የመተላለፍ ችሎታ የለውም ፤ ገድ፤ ጉጉትና ሶፈር የለም" ሲሉ ተናግረዋል።(1)

## በገድ ማመን በሁለት መልኩ ተውሂድን ያብላሻል፡-

1- በአላህ ላይ ብቻ በመመካት ፈንታ በገድ ላይ መመካትና፤

2- ትክክለኛ ባልሆነ ነገርና በብዢታ ማመን ናቸው።

## በገድ አማኙ ሁለት ሁኔታዎች ይኖሩታል፡-

1ኛ- የሚያምንበት ገድ ሲያጋጥመው ያሰበውን ዓላማ ሰርዞ ከተመለሰ ይህ እምነቱ ከተውሂድ ጋር የሚፃረር የገድ እምነት ይሆናል ።

2ኛ- ያመነበት ገድ ሲያጋጥመው ተፅዕኖ ካሳደረበትና ከተረበሸ በዓላማው ላይ ቢፀናም ወንጀልነቱ እንደ መጀመሪያው ባይከብድም ነገር ግን ተውሂድን የሚያጓድልና በግለሰቡ ላይ ችግርን የሚያስከትል እምነት ይሆናል።

## የገድን እምነት ሊያስወግዱ የሚችሉ ነጥቦች፡-

---

(1)ከዚህ የምንረዳው በነኝህ ነገሮች ማመን ለምሳሌ፡- ጉጉት የተባለው ወፍ በጮከበት አካባቢ ሰው እንደሚሞትና ሶፈር በተባለው ወር የተለያዩ ክስተቶች እንደሚከሰቱ ማመን በኢስላም የተከለከለና መሰረተ-ቢስ እምነት መሆኑን ነው።

1ኛ- ቀጣዩን ዱዓ ማድረግ፡-

" اللَّهُمَّ لا يَأْتِي بِالْحَسَنَاتِ إِلا أَنْتَ، وَلا يَدْفَعُ السَّيِّئَاتِ إِلا أَنْتَ، وَلا حَوْلَ وَلا قُوَّةَ إِلا بِكَ" .

" አላሁመ ላ የእቲ ቢልሀሰናቲ ኢላ አንተ ወላ የድፈዑ አሰይኣቲ ኢላ አንተ ወላ ሐውለ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላህ" ትርጉሙም " አላህ ሆይ! መልካምን አንተ እንጂ ማንም ማምጣት(መስጠት) አይችልም። መጥፎን(ጉዳትንም) አንተ እንጂ ማንም መከላከል አይችልም። ባንተ ፍቃድ እንጂ ሀይልና ዘዴ አይጠቅምም " ማለት ነው። አቡ ዳውድ ዘግበውታል።

(( اللَّهُمَّ لَا خَيْرَ إِلَّا خَيْرُكَ وَلَا طَيْرَ إِلَّا طَيْرُكَ وَلَا إِلَهَ غَيْرُكَ)).

" አላሁመ ላ ጦይረ ኢላ ጦይሩከ ወላ ኸይረ ኢላ ኸይሩከ ወላ ኢላሀ ኢላ አንተ " አህመድ ዘግበውታል።

ትርጉሙም፡-" አላህ ሆይ! ገድንና እድልን ወሳኙ አንተ ብቻ ነህ። መልካምንም መስጠትና መቸር የምትችለው አንተ ብቻ ነህ። ትክክለኛ አምላክ ከአንተ በስተቀር የለም።"

2ኛ-በገድ ማመን በተውሂድ ላይ የሚያስከትለውን አደጋ ማወቅና መረዳት።

3ኛ- በአላህ ውሳኔ ማመን።

4ኛ- ራስን መታገልና በአላህ ላይ ጥሩ እምነትንና ጥርጣሬን ማሳደርና።

5ኛ- መልካሙን ነገር አንተ ምረጥልኝ ብሎ አላህን መማፀን ናቸው ።

## <u>አንድ ሰው በገድ አመነ የሚባለው መቼ ነው?</u>

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ አህመድ በዘገቡት ሐዲስ፡-

«إِنَّمَا الطِّيَرَةُ مَا أَمْضَاكَ، أَوْ رَدَّكَ»

“በዓላማህ ላይ እንድትፀና ወይም ከዓላማህ እንድትመለስ ያደረገህ ነገር የገድ እምነት ይባላል” ብለዋል።

## ተስፈኘነት፡-

መልካምን ቃል በመስማት መደሰት ለምሳሌ፡- አንድ መንገደኛ ሰላም የሚል ቃል ሲሰማ መደሰት ተስፈኘነት ይባላል። እሱም የተፈቀደ ነው። የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

"وَيُعْجِبُنِي الْفَأْلُ: الْكَلِمَةُ الْحَسَنَةُ، الْكَلِمَةُ الطَّيِّبَةُ"

“ መልካም ቃል ያስደስተኛል ” ብለዋል።

## በተስፈኘነትና በገድ እምነት መካከል ያለው ልዩነት፡-

1- በአላህ ላይ መጥፎን መጠራጠር፤ አምልኮ የሆነውን ተወኩልን ከአላህ ውጭ ለሆነ አካል አሳልፎ መስጠትና መጥቀምም ሆነ መጉዳት በማይችል ነገር ላይ አዕምሮን ማሳመን የገድ እምነት ሲሆን ፤

2- በዓላማው ላይ ፀንቶ መልካምን ነገር ከአላህ መከጀል ደግሞ ተስፈኘነት ይባላል ።

## * በከዋክብት ዙሪያ ያሉ እምነቶችና አጠቃቀሞች በሁለት መልኩ ይታያሉ፡-

አንደኛው ፡- የተከለከለ ሲሆን እሱም በሦስት ይከፈላል፡-

1- ከዋክብት በራሳቸው ጊዜ ችግሮችንና ክስተቶችን ይፈጥራሉ ብሎ ማመን ከከፍተኛው የማጋራት ወንጀል ይመደባል።

2- በከዋክብት አማካኝነት ከህዋሳት የራቁና የተሰወሩ ነገሮችን አውቃለሁ ብሎ መናገር እንደ ከፍተኛው ክህደት ሲታይ ፣

3- ከዋክብት ለጥሩም ይሁን ለመጥፎ ነገር ምክንያት /ሰበብ ናቸው ብሎ ማመን ደግሞ ከመለስተኛው ማጋራት ይቆጠራል።

ሁለተኛው ፡-ክፍል የተፈቀደ ሲሆን እሱም በከዋክብት አማካኝነት አቅጣጫዎችንና የወራቶችን መለዋወጥ ማወቅ ነው ።

## ከዋክብት ለምን ተፈጠሩ ?

ከዋክብት የተፈጠሩት ለሶስት ዓላማዎች ብቻ ነው እነሱም፡-

1- ለሰማይ ውበትና ጌጥ፤

2- ለሰይጣናት መቀጥቀጫ እና

3- አቅጣጫዎችን ማወቂያ ነው ።

### በከዋክብት ዝናብን መለመን፡-

በከዋክብት ዝናብን መለመን በሁለት ይከፈላል፡-

አንደኛው ፡- ከፍተኛ የማጋራት ወንጀል ሲሆን ይህም በሁለት መልኩ ይገለፃል፡-

1- ከዋክብትን ዝናብ ያዘንቡ ዘንድ በቀጥታ መለመን ለምሳሌ፡- እገሌ የተባልክ ኮከብ ሆይ! ዝናብ ስጠን፤ አዝንብልን ፤አጠጣንና የመሳሰሉትን ቃል በመጠቀም መለመንና፣

2- ከዋክብት በራሳቸው ጊዜ ዝናብን የማዝነብ ችሎታ አላቸው ብሎ ማመን ናቸው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ وَتَجْعَلُونَ رِزْقَكُمْ أَنَّكُمْ تُكَذِّبُونَ }( الواقعة: **82).**

“ በሲሳያችሁ(በዘነበላችሁ ዝናብ)አላህን ማመስገን ሲገባችሁ ታስተባብላላችሁን ? ” (አል-ዋቂዓ: 82)

ሙጃሂድ የተባሉ ዐሊም ይህችን አንቀፅ ሲያብራሩ እገሌ የተባለው ኮከብ አዘነበልን በማለት የአላህን ጸጋ የሚያስተባብሉ ሰዎችን የሚያወግዝ አንቀጽ ነው ብለዋል ።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

**" هَل تَدْرُونَ مَاذَا قَالَ رَبُّكُمْ؟ قَالُوا: اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ، قَالَ: " أَصْبَحَ مِنْ عِبَادِي مُؤْمِنٌ بِي وَكَافِرٌ، فَأَمَّا مَنْ قَالَ: مُطِرْنَا بِفَضْلِ اللَّهِ وَرَحْمَتِهِ، فَذَلِكَ مُؤْمِنٌ بِي وَكَافِرٌ بِالكَوْكَبِ، وَأَمَّا مَنْ قَالَ: بِنَوْءِ كَذَا وَكَذَا، فَذَلِكَ كَافِرٌ بِي وَمُؤْمِنٌ بِالكَوْكَبِ"**

“ ጌታችሁ ምን እንዳለ ታውቃላችሁን ? ሲሉ ሱሃቦችን ጠየቁ እነሱም አላህና መልእክተኛው ያውቃሉ ሲሉ መለሱ። እርሳቸውም እርሱ (አላህ) እንዲህ አለ፡ - ከባሮቼ ከፊሉ በእኔ አማኝ ሆኖ ሲያድር ከፊሉ ከሃዲ ሆነ። በአላህ ችሮታና እዝነት ዘነበልን ያለ በእኔ አማኝ ሲሆን በከዋክብት ከሃዲ ሆነ። እገሌ በተባለው ኮከብ ዘነበልን ያለ ደግሞ በእኔ ከሃዲ ሲሆን በከዋክብት አማኝ ሆነ ” አሉ ።

2- ዝናብ ለመዝነብ ከዋክብት ምክንያት ናቸው ብሎ ማመን መለስተኛ የማጋራት ኃጢአት ሲሆን ዝናብ የሚዘንብበትን ወቅትና ጊዜ በከዋክብት አማካኝነት ማወቅ ግን የተፈቀደ ነው።

## ይስሙላ፡-

አንድን መልካም ስራ ሰዎች አይተው ወይም ሰምተው ያመሰግኑት ዘንድ ይፋ ማድረግና አሳምሮ መስራት ይስሙላ ይባላል እሱም በሁለት ይከፈላል።

1ኛ- ለይስሙላ የሚሰራው አንዳንድ ጊዜና በተወሰኑ አምልኮዎች ብቻ ከሆነ መለስተኛው የማጋራት ወንጀል ሲሆን ፣

2ኛ- ተግባሩ በሙሉ ወይም አብዛኛው ለይዩልኝ (ለዩስሙላ) ከሆነ ግን ከፍተኛው የማጋራት ወንጀል ይሆናል። ይህም የሙናፊቅ ባህሪና ምልክት እንጂ የአማኝ ባህሪ አይደለም ።

## የይስሙላ አደገኝነት፡-

1-ከማጋራት ወንጀሎች አንዱ መሆኑ፡- የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/አል-ኢማሙ አህመድ በዘገቡት ሐዲስ፡-

**«إِنَّ أَخْوَفَ مَا أَخَافُ عَلَيْكُمُ الشِّرْكُ الْأَصْغَرُ» قَالُوا: وَمَا الشِّرْك الأَصْغَرُ يَا رَسُولَ اللَّهِ؟ قَالَ: " الرِّيَاءُ " .**

" በናንተ ላይ ከሚያሰጋኝ ነገር ሁሉ በእጅጉ የሚያሰጋኝ መለስተኛው የማጋራት ወንጀል ነው " ብለዋል። እሱም ምን እንደሆነ ሲጠየቁ" ለይስሙላ መስራት ነው " አሉ።

2- ይስሙላ በተውበት(በንስሓ) እንጂ የማይማር ወንጀል መሆኑ፡- አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ إِنَّ اللَّهَ لا يَغْفِرُ أَنْ يُشْرَكَ بِهِ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَلِكَ لِمَنْ يَشَاءُ وَمَنْ يُشْرِكْ بِاللَّهِ فَقَدِ افْتَرَى إِثْمًا عَظِيمًا } ( النساء : (48).

" አላህ በእርሱ የማጋራትን ወንጀል በፍጹም አይምርም፡፡ ከዚህ ሌላ ያለን (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል፡፡ በአላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኀጢአት በእርግጥ ቀጠፈ"(አኒሳእ: 48)፡፡

ይህ የቁርዓን አንቀፅ የሚያስረዳው ማንኛውም የማጋራት ወንጀል ከፍተኛውም ሆነ መለስተኛው በተውበት/በንስሓ/እንጂ የማይማር መሆኑን ነው።

3- ከእርሱ ጋር ግንኙነት ያለውን መልካም ስራ ማውደሙ፡-

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አላህ እንዲህ ብሏል ሲሉ ተናግረዋል፡-

" أَنَا أَغْنَى الشُّرَكَاءِ عَنِ الشِّرْكِ، مَنْ عَمِلَ عَمَلا أَشْرَكَ فِيهِ مَعِي غَيْرِي، تَرَكْتُهُ وَشِرْكَهُ "

“ እኔ ከአጋር የተብቃቃሁ ነኝ። ስለዚህ አምልኮውን ከኔ ጋር ሌላን አካል በማጋራት የፈፀመ ሰው ከነሽርኩ እተወዋለሁ።”

4- የይስሙላ አደገኝነት ሐሰተኛ ከሆነው አልመሲህ አደጋ የከፋና የበለጠ መሆኑ ናቸው፡-

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ አሊማሙ አህመድ በዘገቡት ሐዲስ፡-

«أَلا أُخْبِرُكُمْ بِمَا هُوَ أَخْوَفُ عَلَيْكُمْ عِنْدِي مِنَ الْمَسِيحِ الدَّجَّالِ؟» قَالَ: قُلْنَا: بَلَى، فَقَالَ: «الشِّرْكُ الْخَفِيُّ، أَنْ يَقُومَ الرَّجُلُ يُصَلِّي، فَيُزَيِّنُ صَلَاتَهُ، لِمَا يَرَى مِنْ نَظَرِ رَجُلٍ)

“ ከደጃል አደጋ ይበልጥ በናንተ ላይ የሚያሰጋኝን ነገር ልንገራችሁን?” አሉ እንዴታ ይንገሩን እንጂ ሲሏቸው፡- “ስውር የሆነው የማጋራት ወንጀል ነው እርሱም አንድ ሰው ሶላት በሚሰግድበት ወቅት ሰዎች ወደ እርሱ የሚመለከቱ መሆናቸውን ሲያውቅ ሶላቱን አሳምሮ መስገድ ነው” አሉ ።

**<u>ይስሙላ ከሥራ ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር በሶስት ይከፈላል</u>፡-**

1-መልካም ስራውን ለመስራት ያነሳሳው ይስሙላ ከሆነ ይህ አስተሳሰቡ(ኒያው) የማጋራት ወንጀል ሲሆን አምልኮውም ተቀባይነት አያገኝም።

2- ስራውን ለአላህ ብሎ ከጀመረው በኋላ የይስሙላ በሽታ ከተከሰተበት ይህ ጉዳይ በሁለት መልኩ ይታያል፡-

ሀ- ራሱን ከታገለና በይስሙላ ላይ ካልቀጠለ በስራው ላይ ምንም ዓይነት ችግር አያሳድርበትም።

ለ- በይስሙላው ደስተኛ ሆኖ በዚያው ላይ ከቀጠለ ደግሞ የሚያደርገውን አምልኮ በሁለት መልኩ ማየት ያሻል፡-

1- በመጨረሻ ያደረገው አምልኮ ከመጀመሪያው ጋር ተያያዥነት ካለው ለምሳሌ፡- ፍጹም ለአላህ አጥርቶ አንድ ረከዓ ከሰገደ በኋላ የሚቀጥለውን ሁለተኛ ረከዓ ለይስሙላ ከሰገደው ሁለቱም ረከዓዎች ይበላሻሉ ።

2- ለይስሙላ የፈፀመው የመጨረሻው መልካም ስራ ከመጀመሪያው ጋር ተያያዥነት ከሌለው ደግሞ ለምሳሌ ፡-ፍጹም ለአላህ ብቻ አጥርቶ አንድ መቶ ብር ለሰደቃ ከሰጠ በኋላ ሰዎች ያመሰግኑት ዘንድ ሌላ አንድ መቶ ብርን ቢሰጥ የመጀመሪያው ሶደቃ ተቀባይነት ሲኖረው የሁለተኛው መቶ ብር ሶደቃ ግን ተቀባይነት አያገኝም።

3- የይስሙላ ስሜት የተሰማው መልካም ስራው ከተፈፀመ በኋላ ከሆነ በአምልኮው ላይ ምንም አይነት ችግር አያሳድርበትም ።

## ማሳሰቢያ፡-

አንድ ሰው በሚሰራው መልካም ስራ ሰዎች ሲያሞግሱትና ሲያመሰግኑት መደሰቱ በሃይማኖቱ ላይ ምንም ዓይነት ችግር አያሳድርበትም። እንዲያውም ሙስሊም እንደዘገቡት ይህ በዚህች ዓለም ቀድሞ የመጣ የአማኙ ብስራት ነው ።

## ማሳሰቢያ፡-

ሰዎች ያዩኛል ወይም ይሰሙኛል በሚል ስጋት መልካም ስራን (አምልኮን) መተውና ማቋረጥ መለስተኛ የማጋራት ወንጀል ይሆናል ።

**- <u>የይስሙላን በሽታ ሊከላከሉ የሚችሉ ወሳኝ ነጥቦች</u>፡-**

1- ፍፁምነት(ለአላህ ብቻ አጥረቶ መስራት) የሚያስገኘውን ደረጃ ማወቅና ማስታወስ፣

2- ለይስሙላ መስራት የሚያስከትለውን የአኺራ ኪሳራ መረዳትና ከልብ መገንዘብ፣

3- ሰዎች መጥቀምም ሆነ መጉዳት እንደማይችሉ ጠንቅቆ ማወቅና

4- በሚከተለው ዱዓ አላህን መማፀን ናቸው እሱም፡-

" اللَّهُمَّ إني أعوذ بك من أن أشرك بك شيئاً أعلمه وأستغفرك لما لا أعلمه ".

“ አላህ ሆይ ! እያወቅኩ ባንተ ከማጋራት ባንተው እጠበቃለሁ በማላውቀው ደግሞ ምህረትህን እጠይቃለሁ።”

**<u>አንድ ሰው በሚሰራው መልካም ስራ/ የቅርቢቱን ህይወት መሻት</u>፡-**

ገንዘብ ለማግኘት ብቻ አስቦ ሐጅ ማድረግ፤ ለምርኮ ገንዘብ ብሎ መዝመት እና የመሳሰሉትን ንጹህ አምልኮዎች ለግዚያዊ ጥቅም ብቻ አስቦ መፈፀም በሁለት መልኩ ይታያል፡-

1- የሚፈፅመው አምልኮ በሙሉ ወይም አብዛኛው የቅርቢቱን ሕይወት ጥቅም ለማግኘት ከሆነ ከፍተኛው የማጋራት ወንጀል ሲሆን ፣

2- ዓለማዊ ጥቅም ለማግኘት የሚያከናውነው አምልኮ የተወሰነ እና ጥቂት ከሆነ ደግሞ መለስተኛ የማጋራት ወንጀል ይሆናል። ለዚሁ ዓላማ ያደረገውም አምልኮ ተቀባይነት አያገኝም።

አንድ ሰው በሚሰራው የአምልኮ ተግባር የዓለማዊ ጥቅምን ብቻ ማሰብ እንደሌለበት የሚያስጠነቅቁ ብዙ ቁርኣናዊ አንቀፆችና ነቢያዊ ሐዲሶች አሉ፡- አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ مَنْ كَانَ يُرِيدُ الْحَيَاةَ الدُّنْيَا وَزِينَتَهَا نُوَفِّ إِلَيْهِمْ أَعْمَالَهُمْ فِيهَا وَهُمْ فِيهَا لا يُبْخَسُونَ (15) أُولَئِكَ الَّذِينَ لَيْسَ لَهُمْ فِي الآخِرَةِ إِلا النَّارُ وَحَبِطَ مَا صَنَعُوا فِيهَا وَبَاطِلٌ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ } هود: 16)

" በሚሰሩት መካም ሥራ የቅርቢቱን ሕይወትና ውበቷን የሚሹ ሰዎች ሙሉ የስራ ውጤታቸውን በዱንያ ላይ እያሉ እንከፍላቸዋለን። እነሱም በእርሷ ላይ እያሉ አይጓደልባቸውም። እነዚያ እነርሱ በመጭዋ ዓለም እሳት እንጂ የላቸውም" (ሁድ: 16)።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ አህመድና አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ፡-

((مَنْ تَعَلَّمَ عِلْمًا مِمَّا يُبْتَغَى بِهِ وَجْهُ اللَّهِ عَزَّ وَجَلَّ لا يَتَعَلَّمُهُ إِلا لِيُصِيبَ بِهِ عَرَضًا مِنَ الدُّنْيَا، لَمْ يَجِدْ عَرْفَ الْجَنَّةِ يَوْمَ الْقِيَامَةِ ))

" ለአላህ ፊት ብሎ መማር ያለበትን የሃይማኖት እውቀት ለዱንያ ጥቅም ብሎ የተማረ ሰው የጀነትን ሽታ አያገኝም " ብለዋል ።

## መሐላ፡-

አላህ፣ አረህማን፣ አልዐዚም፣ አሰሚዕ በሚሉት በአላህ ስሞች እና እንደዚሁም በእዝነቱ፤ ባሸናፊነቱ፤ በእውቀቱና በመሳሰሉት ባህሪያቱ መማል የተፈቀደ ሲሆን ከአላህ ሌላ በሆነ አካል መማል የተከለከለ ነው ።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ አሊማሙ አህመድ፤ አቡ ዳውድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ፡

((مَنْ حَلَفَ بِغَيْرِ اللَّهِ فَقَدْ أَشْرَكَ))

" ከአላህ ሌላ በሆነ አካል የማለ ሰው በእርግጥ ካደ ወይም አጋራ" ብለዋል።

ከአላህ ውጭ በሆነ አካል መማል በሁለት መልኩ ይታያል፡-

1- ከአላህ ውጭ የሚምልበትን አካል እንደ አላህ ወይም ከአላህ በላይ የሚያከብረው ከሆነ ከፍተኛው (ትልቁ) ሽርክ ሲሆን ፣

2- የሚምልበትን አካል እንደ አላህ የማያከብረው ከሆነ ደግሞ መለስተኛው( ትንሹ) ሽርክ ይሆናል።

## <u>ከአላህ ውጭ ያለ- አግባብ የሚማልባቸው ነገሮች</u> ፡-

ነቢያት፤ደጋግ ሰዎችና ወላጆች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ። በእነዚህና በመሳሰሉት ነገሮች መማል የተከለከለ ነው።

<u>ከዚህ ርእስ የምንማራቸው ጠቃሚ ነጥቦች</u>፡-

1- ከአላህ ሌላ በሆነ አካል መማል የማጋራት ወንጀል መሆኑን፤

2- በአላህ ስም በሀሰት መማል የተከለከለ መሆኑን፤

3-አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር በአላህ ስም ብዙ ጊዜ መማል የማይፈቀድ መሆኑንና

4- አስፈላጊ ከሆነ በአላህ ስም መማል የተፈቀደ መሆኑን ነው።

## <u>ከአላህ ውጭ በሆነ አካል የማለ ሰው ለመሐላው ማስረዥ ምን ማለት አለበ?</u>፡-

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

" مَنْ حَلَفَ فَقَالَ فِي حَلِفِهِ: وَاللاتِ وَالعُزَّى، فَلْيَقُلْ: لاَ إِلَهَ الا اللهُ "

“ በላትና በዑዛ የማለ ሰው ላኢላህ ኢለላህ ( ከአላህ በስተቀር በሀቅ የሚገዙት አምላክ የለም) ይበል” ብለዋል። ላትና ዑዛ የተባሉት የጣዖት ስሞች ናቸው።

**<u>አላህንና ፍጡርን (እና) በሚለው አያያዥ ቃል ማጋራት</u> ለምሳሌ፡-**

1- በአላህና ባንተ ፈቃድ ይህ ነገር ተሳካ፤

2- በአላህና በአንተ ላይ ተስፋ አደርጋለሁ፣

3- ከአላህና ካንተ በስተቀር ለእኔ ማን ደራሽ አለኝ፣

4- ከአላህ ፍቃድ ጋር ይህ ነገር ይጠቅማል፤

አንድ ሰው እነዚህንና የመሳሰሉትን ቃላት ሲጠቀም ከአላህ ውጭ የሆነ አካል ከአላህ ጋር እኩል መሆኑን የሚያምን ከሆነ እምነቱ ከፍተኛው የማጋራት ወንጀል ሲሆን ይህ እምነት ከሌለው ደግሞ መለስተኛው የማጋራት ወንጀል ይሆናል።

ነገር ግን መባል ያለበት ነገሮችን ሁሉ ወደ አላህ በማስጠጋት፡- በአላህ ፍቃድ እንዲህ ሆነ፤ በአላህ ላይ ብቻ ተስፋ አደርጋለሁ፤ አላህን ብቻ እገዛ እጠይቃለሁ ይህም አባባል የበለጠና የተሻለ ቢሆንም አላህን እገዛ እጠይቃለሁ ከዚያም አንተን ማለትም ይፈቀዳል።

**<u>ማሳሰቢያ፡-</u>**

(እና) በሚለው አያያዥ ቃል የተጠቀሱ ነገሮች መጀመሪያ ከተጠቀሰው ነገር ጋር በተፈለገው ጉዳይ ላይ እኩል መሆናቸውን ስንረዳ (ከዚያም) በሚለው አያያዥ ቃል የተጠቀሱ ነገሮች ግን መጀመሪያ ለተጠቀሰው ነገር ተከታይ መሆናቸውን እንረዳለን።

## <u>እንዲህ ቢሆን(ባይሆን) ኖሮ ይህ ባልሆነ ነበር ማለት፡-</u>

እነዚህን ቃላት መጠቀም በሁለት ተከፍሎ ይታያል፡-

1- ለመልካም ስራ ያለውን ጉጉትና ምኞት ለመግለፅ ከሆነ ለምሳሌ፡- ገንዘብ ቢኖረኝ ኖሮ አላህ በሚወደውና በሚፈልገው መንገድ ላይ ባዋልኩት ነበር

ብሎ መመኘት የተፈቀደና ብሎም የተመሰገነ ይሆናል። የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ አንድ ሰው፡-

لَوْ أَنَّ لِي مَالا لَعَمِلْتُ بِعَمَلِ فُلَانٍ فَهُوَ بِنِيَّتِهِ فَأَجْرُهُمَا سَوَاءٌ،

“ ገንዘብ ቢኖረኝ ኖሮ እንደ እገሌ መልካም በሰራሁ ነበር ሲል ሰሙት።  ይህ ሰው በመልካም ምኞቱ  መልካም ከሰራው ጋር እኩል ምንዳ አገኘ ” አሉ።

2- ቃሉን የተጠቀመው የአላህን ህግና ውሳኔ ለመቃወም ወይም ለወንጀል ያለውን ፍላጎት ለመግለፅ ከሆነ የተከለከለ ይሆናል። መናፍቃን የአላህን ውሳኔ ለመቃወም በጦርነት የተገደሉትን ሰዎች አስመልክተው “ቢታዘዙን ኖሮ ባልተገደሉ ነበር” “ ከእኛ ዘንድ ቢሆኑ ኖሮ ባልሞቱና ባልተገደሉ ነበር ” አሉ። የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ አንድ ሰው ወንጀልን በመመኘት፡-

" لَوْ أَنَّ لِي مَالا لَعَمِلْتُ فِيهِ بِعَمَلِ فُلانٍ فَهُوَ بِنِيَّتِهِ فَوِزْرُهُمَا سَوَاءٌ "

“ ገንዘብ ቢኖረኝ ኖሮ እንደ እገሌ በሰራሁ ነበር ሲል ሰሙት ። ይህ ሰው ክፉ በማሰቡ ብቻ  ወንጀል ከሰራው ጋር እኩል ናቸው ” አሉ።

## ግዜን መሳደብ እና መተቸት፡-

ግዜን መሳደብ( መተቸት) በሶስት ተከፍሎ ይታያል፡-

1- ግዜውን ለመሳደብ ወይም ለመተቸት ሳይሆን በግዜው ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለመናገር ከሆነ ለምሳሌ፡- የዚህ ቀን ወይም ወር ሙቀት ወይም ብርድ አሰቃየን ማለት ነቢዩላህ ሉጥ  “ይህ አደገኛ ቀን ነው ” እንዳሉት ሁሉ የተፈቀደ ይሆናል ።

2-ግዜውን አድራጊና ፈጣሪ አድርጎ በማሰብ መሳደብና መውቀስ እንደ ትልቁ ሽርክ የሚቆጠር ከባድ  ወንጀል ነው ።

3- አድራጊና ፈጣሪው አላህ ብቻ መሆኑን እያመነ የሚጠላቸው ነገሮች በግዜው ውስጥ ስለሚፈራረቁ ብቻ ግዜን መሳደብና መተቸት ከታላላቅ ወንጀሎች የሚቆጠርና አላህን እንደመረበሽ የሚታይ እኩይ ተግባር ነው። የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አላህ እንዲህ ይላል ብለዋል፡-

" يُؤْذِينِي ابْنُ آدَمَ يَسُبُّ الدَّهْرَ وَأَنَا الدَّهْرُ، بِيَدِي الأَمْرُ أُقَلِّبُ اللَّيْلَ وَالنَّهَارَ"

“ የአደም ልጅ ግዜን በመሳደብ ሊረብሸኝ ይሞክራል ሁሉም ነገር በእጄ ነው ሌሊትንና ቀንን አፈራርቃለሁ ። ”

## <u>ቃላት አጠቃቀምን በተመለከተ ሁለት ጠቃሚ ነጥቦች አሉ፡-</u>

1- ውሸት መናገር፤ ወሬ ማናፈስ፤ ሐሜት፤ ከአላህ ውጭ በሆነ አካል መማልና የመሳሰሉት የተከለከሉ ስለሆኑ ከእነዚህ ነገሮች ምላሶቻችንን መቆጠብ ያስፈልጋል። ምክንያቱም አንድ ሰው በተናገረው ነገር ሁሉ ተጠያቂ ስለሆነ ነው። ሌላው ደግሞ አንድ ሰው ግምት ሳይሰጠው በሚናገረው ቃል ሳቢያና መዘዝ ከኢስላም የሚወጣበት አጋጣሚ ሊፈጠር ስለሚችል ቃላትንና ፊደሎችን ስንጠቀም ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል።

2- ከማጋራት ወንጀል ላይ የሚጥሉ ቃላትንና ፊደሎችን ከመጠቀም መቆጠብ ያስፈልጋል ።

## <u>ፈጠራ፡-</u>

ቢድዓ (ፈጠራ) በሁለት ይከፈላል፡-

1- የቅርቢቱን ሕይወት በጥሩ ሁኔታ ለመኖር የሚያስችሉና የሚረዱ ነገሮችን መፍጠርና መስራት በኢስላም የተፈቀደና የተበረታታ ሲሆን፣

2- በሃይማኖት ጉዳይ የሚፈጠሩ ፈጠራዎች በሙሉ የተከለከሉና የተወገዙ ናቸው። ምክንያቱም ሃይማኖት ከአላህና ከመልእክተኛው የመጣውን ህግና ስርዓት መከተል እንጂ አዲስ ነገር መፍጠርና መጨመር ስለማይቻል ነው።

**<u>በሃይማኖት ዙሪያ የሚፈጠሩ ፈጠራዎች በሶስት ይከፈላሉ።</u> እነሱም፡-**

1- እምነታዊ ፈጠራ ሲሆን እሱም አላህና መልእክተኛው በተናገሩት ተቃራኒ ማመን ነው። ለምሳሌ፡- የአላህን ስሞችና ባህሪያት ከፍጥረታት ስሞችና ባህሪያት ጋር ማመሳሰል፤ አዛብቶ መተርጎም ወይም ትርጉም አልባ ማድረግና አላህ ማንኛውንም ነገር ቀደም ሲል መወሰኑን አለመቀበል።

2- ተግባራዊ ፈጠራ ነው። እሱም አላህ ባላወረደው ህግና የነቢዩ ሙሀመድ /ﷺ/ አስተምህሮት በሌለበት ሁኔታ አላህን መገዛት ሲሆን ይኸውም በበርካታ ነገሮች ይገለፃል።

1- በኢስላም የማይታወቅ አምልኮ መፍጠር ለምሳሌ ፡- በቀብር ዙሪያ መዞር፤ የተለያዩ ባእሎችን መፍጠርና ማክበር፤

2- መጨመርም ሆነ መቀነስ በማይፈቀድባቸው አምልኮዎች ላይ መጨመር ወይም መቀነስ፤

3- በተለየ ወቅት መፈፀም ያለበትን አምልኮ ሌላን ወቅት ፈጥሮ ማከናወን ወይም  በአዲስ አሰራር መፈፀም፤

4- የተፈቀዱ ነገሮችን ለምሳሌ፡- ስጋ መብላት፤ ማግባት መተኛትና የመሳሰሉትን ራሱን ለመቅጣትና አምልኮ(ዒባዳ) ይሆናል በሚል ስሜት አለመጠቀምና የመሳሰሉት ናቸው።

**<u>ቢድዓ (ፈጠራ) ሁለት ዓይነቶች አሉት።</u> እነሱም፡-**

1- ከኢስላም የሚያስወጣ የቢድዓ ዓይነት ነው ። ለምሳሌ፡- ቁርኣን የአላህ ቃል መሆኑን በማመን ፈንታ የአላህ ቃል አይደለም ብሎ ማመን፣

2- ከኢስላም ባያስወጣም ነገር ግን አመፀኛና ወንጀለኛ የሚያሰኝ የቢድዓ ዓይነት ነው።  ለምሳሌ፡- ተሰባስቦ በአንድ ድምፅ አላህን መዘከር ወይም

ማወደስ፤ ከሻዕባን ወር አስራ አምስተኛዋን ሌሊት ነቅቶ ማሳለፍ እና የመሳሰሉት ናቸው ።

## ፈጠራን (ቢድዓን)የሚያወግዙና የሚያስጠንቅቁ የቁርኣን አንቀፆችና ሐዲሶች፡-

አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا } ( المائدة : 3 )

“ በዛሬው ዕለት ለእናንተ ሃይማኖታችሁን አሟላሁላችሁ ፀጋዬንም በእናንተ ላይ አትረፈረፍኩ ለእናንተም ከሃይማኖት ኢስላምን ወደድኩላችሁ” (አል-ማኢደህ: 3)

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

«مَنْ أَحْدَثَ فِي أَمْرِنَا هَذَا مَا لَيْسَ فِيهِ، فَهُوَ رَدٌّ»

“ በሃይማኖታችን ጉዳይ ከእርሱ ያልሆነን ነገር የፈጠረና የጨመረ ሰው ፈጠራው ተመላሽ ነው ” ሙስሊም በሌላ ዘገባቸው “ ፍቃዳችን የሌለበትን ሥራ በአምልኮ ስም ያከናወነ ሰው ስራው ውድቅ (ተመላሽ) ነው ” ብለዋል ።

በሌላ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስም፡-

“ ከነገሮች ሁሉ አስቀያሚ ማለት በሃይማኖት ጉዳይ የሚፈጠሩ ነገሮች ናቸው”፣ “ ማንኛውም ፈጠራ ጥሜት ነው ” ብለዋል።

አል ኢማሙ ማሊክ የተባሉ ዓሊም “ በኢስላም አንድን ቢድዓ (ፈጠራ) መልካም ነው በሚል እሳቤ የፈጠረ ሰው ነቢዩ ሙሀመድ /ﷺ/ ተልዕኳቸውን አላደረሱም እያለ መሆኑ አያጠራጥርም። በነቢዩ ዘመን ሃይማኖት ያልሆነ ነገር ዛሬ ሃይማኖት ሊሆን አይችልም ” ሲሉ ተናግረዋል ።

## በኢስላም ጥሩ ፈጠራና መጥፎ ፈጠራ የሚባል አለን?

በሃይማኖት ጉዳይ የሚፈጠሩ ፈጠራዎችን ጥሩና መጥፎ ብሎ መከፋፈል (ማንኛውም ፈጥራ ጥመት ነው ) ከሚለው ነቢያዊ ሐዲስ ጋር የሚጋጭ የተሳሳተ አባባል ነው። ምክንያቱም ሐዲሱ ማንኛውም በሃይማኖት ጉዳይ የሚደረግ ፈጠራ ጥመት መሆኑን በግልፅ ያስረዳል።

## ለቢድዓ/ ፈጠራ/ ምክንያት የሆኑ ነገሮች፡-

ሀ- ስለሃይማኖት አለማወቅ፣

ለ- ስሜትና ዝንባሌን መከተል፤

ሐ- ሀቅን በመቀበልና በመከተል ፈንታ ለተለያዩ ግለሰቦችና አስተያየቶች መወገን፣

ሠ- ከሃዲዎች ጋር መመሳሰል፣

ረ- መሰረተቢስና የተቀጠፉ ሐዲሶችን ማስረጃ ማድረግ፤

ሰ- ሃይማኖታዊ ማስረጃም ሆነ ንፁህ አእምሮ የማይደግፋቸውን ባህሎችና ልማዶችን ሙጥኝ ብሎ መያዝና የመሳሰሉት ናቸው።

## አንድ ነገር ፈጠራ መሆኑን ለማወቅና ለቢድዓ ባለቤት በቂ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ወሳኝ ነጥቦች ፡-

1-የአምልኮ ዋና መነሻና መድረሻ ማስረጃ ነው። ስለዚህ ማስረጃ የሌለውን ነገር በአምልኮ ስም ከመፈፀም መታቀብና መቆጠብ ከቢድዓ/ ከፈጠራ/ ለመዳን ዋና መሰረት ነው።

2- አንድ አምልኮ እንዲፈፀም የሚያስችል  በነቢዩ /ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም/ ዘመን በቂ ምክንያት እያለው እሳቸውም ሆኑ ባልደረቦቻቸው ይህን ነገር አለመፈፀማቸው ይህ አምልኮ ፈጠራ መሆኑን በትክክል መረዳት ይቻላል።2

## <u>በሙስሊሙ ማህበረሰብ  ውስጥ በዝተውና ተሰራጭተው የሚስተዋሉ ፈጠራዎች፡</u>

1- የነቢዩንም ሆነ የሌሎችን ግለሰቦች ልደት ማክበር፤

2- የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ወደ ሰማይ የወጡበትን (የሚዕራጅን) ሌሊት ነቅቶ በዒባዳ ማሳለፍ፤

3- ከሸዕባን ወር አስራ አምስተኛዋን ሌሊት ማክበር፤

4- ከሙታንም ሆነ በሕይወት ካሉ ግለሰቦች፤ ከስፍራዎች፤ ከቅርሶችና ከመሳሰሉት ነገሮች  በረከትን(ረደኤትን) መፈለግ ፣

5- በህብረት አላህን መዘከር/ ማወደስ/፣

6- በአስከሬንና  በቀብር ላይ ወይም በተለያዩ አጋጣሚዎች ከቁርኣን ውስጥ የተለያዩ ምእራፎችንና አንቀፆችን ማንበብ ወይም ሰዎችን እንዲያነቡ መጠየቅ፣

7- ሶላት ለመስገድ ሲያስብ የሶላቱን ዓይነት፤ የረከዓዎችን ብዛት፤ ብቻውን ወይም በጀማዓ እንደሚሰግድ በአንደበቱ መናገር፤

8- አላህ ሆይ!  በገሌ ወልይ ወይም በገሌ ሸይኽ  ይሁንብህ እያሉ አላህን መማፀንና የመሳሰሉት ናቸው ።

## <u>ማሳሰቢያ፡-</u>

---

2 ለዚህም መውሊድን እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል። ምክንያቱም መውሊድን ለማውጣት ዋናው ምክንያት የነቢዩ /ﷺ/ መወለድ ነው። ይህ ምክንያት በዘመናቸው ነበር። ታዲያ ልድታቸውን አከበሩ ወይስ አላከበሩም? ካከበሩም በምን መልኩ?

አንድ አምልኮ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ሁለት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1ኛ- ሙታበዓ (መከተል) ሲሆን እሱም አላህን ስንገዛ በመልእክተኛው አማካኝነት በተዘረጋው ህግ መሰረት ብቻ መወሰንና

2ኛ- አምልኮን ለይስሙላ ሳይሆን ፍፁም ለአላህ ብቻ አድረጎ ማከናወን ናቸው።

## ማሳሰቢያ፡-

ሙታበዓ(መከተል) የተባለው መስፈርት ይረጋገጥ ዘንድ የሚፈፀመው አምልኮ በስድስት ነገሮች ከሃይማኖቱ ህግና ደንብ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት እነሱም፡-

1- በምክንያቱ፤
2- በዓይነቱ፤
3- በብዛቱ፤
4- በአፈፃፀሙ፤
5- በግዜው እና
6- በስፍራው ናቸው።

## ወደ ተውሂድ ጥሪ ማድረግ፡-

ወደ ተውሂድ ጥሪ ማድረግ ትልቅ ደረጃ ያለው የነቢያትና የመልዕክተኞች እንደዚሁም የተከታዮቻቸው የሥራ መስክ ነው። ይህም ትልቅ ሥራ አመርቂ ውጤት ያመጣ ዘንድ አላህ ያስቀመጣቸውን የዳዕዋ ስልቶችና የመልእክተኛውን የዳዕዋ አስተምህሮት መከተል ይበጃል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ ادْعُ إِلَى سَبِيلِ رَبِّكَ بِالْحِكْمَةِ وَالْمَوْعِظَةِ الْحَسَنَةِ وَجَادِلْهُمْ بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ } النحل :**125**)

" ወደ ጌታህ መንገድ በጥበብና በጥሩ ተግሳፅ ጥሪ አድርግ በመልካሟም ተከራከራቸው " (አነህል: 125)

አላህ በሌላ አንቀፅ ላይ እንዲህ ይላል፡-

{ قُلْ هذِهِ سَبِيلِي أَدْعُو إِلَى اللَّهِ عَلَى بَصِيرَةٍ أَنَا وَمَنِ اتَّبَعَنِي وَسُبْحَانَ اللَّهِ وَمَا أَنَا مِنَ الْمُشْرِكِينَ } ( يوسف : **108**).

" ይህች መንገዴ ናት ወደ አላህ እጠራለሁ እኔም የተከተለኝም ሰው በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን አላህም በእርሱ ከሚያጋሩት ነገር የፀዳ ነው እኔም ከአጋሪዎች አይደለሁም በል" (ዩሱፍ : 108)

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡-

((فَوَاللَّهِ لأَنْ يهدي الله بِكَ رَجُلا وَاحِدا خَيْرٌ لَكَ مِنْ حُمْرِ النَّعَمِ»

" በአላህ እምላለሁ አንድን ሰው አላህ በአንተ አማካኝነት ቀናውን መንገድ ቢመራው ለአንተ ብዙ ቀያይ ግመሎችን ከማግኘት ይበልጣል" አሉት።

በሌላ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስም፡-

« مَنْ دَعَا إِلَى هُدًى، كَانَ لَهُ مِنَ الْأَجْرِ مِثْلُ أُجُورِ مَنْ تَبِعَهُ، لَا يَنْقُصُ ذَلِكَ مِنْ أُجُورِهِمْ شَيْئًا، وَمَنْ دَعَا إِلَى ضَلَالَةٍ، كَانَ عَلَيْهِ مِنَ الْإِثْمِ مِثْلُ آثَامِ مَنْ تَبِعَهُ، لَا يَنْقُصُ ذَلِكَ مِنْ آثَامِهِمْ شَيْئًا ».

" ወደ ቀና  መንገድ ጥሪ ያደረገ ሰው የተከታዮቹ ምንዳ ሳይቀነስ እነሱ የሚያገኙትን አጅርና ምንዳ ያህል ያገኛል ወደ ጥመት ጥሪ ያደረገም የተከታዮቹ

ወንጀል ሳይቀነስ በተከታዮቹ ላይ የተፃፈው ወንጀል በእርሱ ላይ ይፃፍበታል" ብለዋል ።

ተውሂድ ከማንኛውም ነገር ቅድሚያ መታወቅ ያለበትና ወደ እርሱ ጥሪ ሊደረግለት የሚገባው የመጀመሪያ ግዴታ ነው።

የአላህ መልእክተኛ /ﷺ/ ሙዓዝ የተባለውን ታላቅ ሱሀቢ(ባልደረባ) ወደ የመን አገር ላስተማሪነት ሲልኩት፡-

«إِنَّكَ تَأْتِي قَوْمًا مِنْ أَهْلِ الْكِتَابِ، فَادْعُهُمْ إِلَى شَهَادَةِ أَنَّ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَأَنِّي رَسُولُ اللهِ»

" አንት መጽሐፍ የተሰጣቸውን ሰዎች ታገኛለሕ በቅድሚያ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ አለመኖሩንና እኔ የአላህ መልእክተኛ መሆኔን አስተምራቸው " አሉት።

## <u>ወደ ተውሂድ ጥሪ ለማድረግ ከሚያግዙ ነገሮች፡-</u>

1- ከባለ- ሐብቶች ጋር በመተባበር የተውሂድ መፃሕፍትና ካሴቶችን አባዝቶ ለሰዎች እንዲደርሱ ማድረግ፣

2- ሰዎች በተውሂድ ዙሪያ ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማስተማር፣

3- ልጆችን በተውሂድ ኮትኩቶ ማሳደግ፣

4-ኮርሶችንና ሙሃደራዎችን በማካሄድ የተውሂድን ወሳኝነት ለሰዎች ማስረዳት እና የመሳሰሉት ናቸው።

በመጨረሻም በእዝነቱና በችሮታው ይህን የተውሂድን መጽሐፍ በመተርጎም ለትልቅ ስራ ተሳታፊ ላደረገኝና ላበቃኝ ለአላህ ሰማያትንና ምድርን የሞላ ምስጋና ይገባው እያልኩ ይህን መጽሐፍ በማሳተምና በማባዛት ትብብሩን ላበረከተና በትርጉሙ ዙሪያ ገንቢና ጠቃሚ አስተያየቶን ለለገሰን ሁሉ አላህ ጥሩ ምንዳና ምህረት እንዲከፍለው ዱዓችን ነው።

በአላህ ፍቃድ  እንደ- ሂጅራ አቆጣጠር በ17\06\1435 ላይ ተፈጸመ

وصلى الله على نبينا محمد وعلى آله  وصحبه  وسلم تسليما كثيرا

حقوق الطبع محفوظة للمترجم

የማሳተም እና የማባዛት መብቱ ለተርጓሚው የተጠበቀ ነው ።